አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# ምገባ ኤጀንሲ

Addis Ababa City Administration

# Feeding Agency



## ክብርት ከንቲባ
### አዳነች አቤቤ

የቀደምት ስልጣኔ በለቤት ፤የሰው ዘር መገኛ ምድር … የእኛይቷ ሀገር ኢትዮጵያ … በገዛ የራሳችን የዘመን አቆጣጠር በ1977 ዓ.ም በአስከፊ የርሃብ አደጋ ተመታች።

በበርካታ ሰበብ ምክንያቶች … እንደህዝብ የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ … ተፈጥሮም ጨክና --ከአራሽ ገበሬው ጓዳ … ለዘር የሚሆን እፍኝ እህል ጠፍቶ … በርሃብ የገረጡ ጨቅላዎች ፤ክው ያለ … መሬት … የዘጠፈ ወንዝ … በእሳት የሰለሉ እንስሳት … በያሉበት ወደወቀው … በአለም አደባባይ ታዩ! መሪር ሀዘን፣ስንፍናን በቁጣና መሃት ያሳበቡ ሃሳቦች እዚህና እዚያ ተሰሙ።

ግና … ማሳበቡም ሆነ ቁጣው ሆድ ሊሞላ አልቻለም … ከተረፈ ሳይሆን ካለው የማካፈል እሴት ዕሳቤ ብንሆንም … እንኳን ለሌላ ወገን … ለገዛ ራስና ለቤተሰብ ማቅመስ አለመቻላችን ፈጠጠ፤

እነቦብ ሩልደፍ (ድምጻዊ) “We are the World” አቀንቀነው ከርሀብ ሊታደጉን በዓለም መድረክ ላይ የታረዘን የልጆች ምስል ከፍ አድርገው ይዘው አቀነቀኑ … ገናናዋ ቀደምት ምድር፤ ኢትዮጵያ ‹‹ርሃብ ተምሳሌት›› ተብላ በመዝገባ ቃላት ላይ ተከተበች።

### እነሆ … ዛሬ …

‹‹በብራዚል ሪዩ ዴጄኔሮ “Food to feed the climate justiciurban food solutions for af-aire world” በሚል በተዘጋጀው መድረክ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ133 ከተሞች ጋር ተወዳዳሪ በትምህርት ቤቶች የምገባ መርሃ ግብር PMUFPP (Milan Urban Food Policy Pact) በዘላቂ አመጋገብና ሥነ ምግብ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዲስ አበባ አሸናፊ ሆነች።

ጥቅምት 17/2022 /እ.ኤ.አ አዲስ አበባ አሸነፈች፣ለያውም በምርጥ ተሞክሮ የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም እውቅና አገኘች።

### ታሪክ ተቀየረ

በ77 በዓለም አደባባይ እንዳልተለመነልን በ2014 ተማሪዎቻችን ዓመት ሙሉ መግቦ በማስተማርና ለውጤት በማብቃት ዓለም ዕውቅናን ቸረን።

‹‹ይህንን ሽልማት ያሸነፈች ብቸኛ የአፍሪካ ሀገር ኢትዮጵያ ናት! ስለዚህ ሽልማቱ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካንም ይወክላል። ኢትዮጵያን በብዙ መንገድ ሁል ጊዜ ምግብ የምትለምን ሀገር ተደርጋ የምትታወቅበትን ገፅታ ቀይሮ ዛሬ የደረስንበት፣ በምገባ ፕሮግራም በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ማግኘት ሀገራችንም ታሪካዊ ለውጥ ነው።

ጉዳዩ ሀብታም ወይም ድሃ የመሆን ጉዳይ ሳይሆን፣ የመንግስት፣ የፖሊሲ፣ የተግባርም ቆራጥነትና ካለው ውስን ሃብት ለዜጎች ቅድሚያ በመስጠት በተሰራው ስራ የተገኘ ሽልማት ነው። በዚህ ስራ ውስጥ የደከማችሁ፣ የለፋችሁ፣ ሀሳብ ያፈለቃችሁ፣ ያስተባበራችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ››



## ክብርት ወ/ሮ ቡዜና አልቃደር

የአዲስ አበባ ም/ቤት አፈ-ጉባኤ

‹‹የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራማችን በርካቶች በርሃብ ይወድቁበት ከነበረበት ሁኔታ ወጥተው በተረጋጋ መልኩ የሚማሩበት፣ መጠነ ማቋረጥ የቀነሰበት፣ የውጤት መሻሻል የታየበት፣ ውላጆች ከብዙ ጭንቀት እፎይ ያሉበት ነው››

### ‹‹አዲስ አበባ ሰራች፤ ተሸለመች፤ ተወደሰች።››

... በርካታ ዜጎችን ከጎዳና አንስታ በነፃ እንዲመገቡ ማድረግ ችላለች። ለዚህም ማዕከላትን ከፍታለች፤ በትምህርት ቤቶች ከዕውቀት ባሻገር ገበታ ዘርግታ ማዕድ አቅርባለች። ... ይህ ሰው ተኮር ልማቷ የከተማችን ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ከማድረግ በዘለለ ለዓለም ከተሞች ተሞክሮ ሆነዋል፤ በዓለም አቀፍ መድረክም ዕውቅና አስገኝቶላታል።

ይህ የተቀናጀ ቁርጠኛ አመራር ውጤት ነውና ሀሳቡን የጠነሰሱ ሆነ ሀሳቡን ተቀብለው የደገፉ እጃቸውን የዘረጉ ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል።ከተማችን ራስና መሪ የሆኑ ከንቲባ አዳነች አበቤ በተገኘው ስኬት ... እንኳን ደስ አለዎት እላላሁ!››



## ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሀላፊ

በትምህርት ስራችን ነገን አልመን በልጆች አዕምሮ ላይ የምናስቀምጠው ፍሬ ለትውልደ መለወጥና ለሀገር እድገት የሚጫወተው አበርክቶ ከፍተኛ በመሆኑ በየደረጃው የምናደርገው ርብርብ አጠናክረን ልንቀጥል ይገባል።

ከምንጊዜውም በላይ በትምህርት ስራ ውስጥ የምንገኝ አካላት በሙሉ የከተማ አስተዳደሩ ከለውጡ ወዲህ በዘርፉ ላይ ያስመዘገባቸው ውጤቶች እንዲጎለብቱና በቀጣይም የሚሰሩ ስራዎች ጤታማ እንዲሆን ጉልህ ሚና ልንጫወት ይገባል።

## ወ/ሮ ዘይነባ ሽኩር

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የሴቶች ፣ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ስብሳቢ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ በትምህርት ቤት እና በተስፋ ብርሃን ምገባ መዓከላት እየተሰራ ያለው የምገባ ፕሮግራም የዜጎችን መሃበራዊና ኢኮነሚያዊ ችግር በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተወጣ ያለ ተቋም በመሆኑ ሊደገፍ እና ሊበረታታ ይገባል።






## ፌሪክያ ካሳሁን

የሸገር ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ

በትምህርት ዘርፍ የፊንፊኔ ከተማ አስተዳደር ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ ለተማሪዎች ምግብ፣ የትምህርት ቁሳቁስ፣ የተማሪዎች ዩኒፎርም እና የመምህራን ዩኒፎርም በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መድቦ ሲሰራ ቆይተል።

ከፊንፊኔ ከተማ ጋር የተደረገው የማስተባበር ፕሮግራም የተባረከ ውጤታማ ህዝባችንን ተጠቃሚ ያደረገ ፕሮግራም ነው። ለዚህ ተግባር ስኬትና ለዚህ የተባረከ ፕሮግራም ዉጤት ልዑል አምላክን እያመስግንኩ በመቀጠል የከንቲባ ጽ/ቤትን በተለይም ክቡርት አዴ አዳነች አቤቤን እና የምግብ ኤጀንሲን ፣አመራሮቻቸውንና ባለሙያዎችን እንዲሁም የትምህርት ቢሮን ጨምሮ ከልብ አመሰግናለሁ።




የሀገሪዊ ለውጥ፣ የመሪዎች አስተዋይነት
ብሎም ውሳኔ ሰጪነት እና የቀና ልቦች ትብብር
የወለደው የሰው ተኮር ተግባር ...

## ምገባ!

## አንቺነሽ ተስፋዬ አየለ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ
ዋና ዳይሬክተር

ለተማሪዎች ልዩ ዕድል ፈጥሮ ባዶ ምሳ ዕቃ ያስጣለ፣ ለወላጆች እፎይታ ሆኖ ልጆቻቸውን ሁሉ ወደ ት/ቤት እንዲልኩ ያደረገ፣ ለመምህራን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ለመማር ማስተማር ሥራው የሚያግዝና ት/ቤት የሚወደድ ቦታ እንዲሆን ያስቻለ፣ በተመሳሳይ  የትምህርት ግብአትና የደንብ ልብስ ስለሚመገቡት ነገር ምንም ሳይጨነቁ ሃሣባቸውን ሁሉ ትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲሆን ያደረገው የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር!

አለኝታነት፣ ወገን መሀል መኖርን እና የመሪዎችን ርህራሄ ማሳያ የሆነው ደግሞ የዕለት ጉርስ አጥተው ከቆሼ ላይ ምግብ ለማንሳት የተዘረጉ እጆችን በመሰብሰብ በተዘጋጀ ንጹህ ቦታ ትኩስ ምግብ በተገቢው የሚቀርብባቸው የተስፋ ብርሐን የምገባ ማዕከላት!

እነዚህን ሰው ተኮር ተግባራት ሲከናወኑ ዕድሉን አግኝቼ በማስተባበሬና በመምራቴ በጣም ደስተኛ ነኝ!  ነገ በበለፀገች ሀገር ለትውልድ የምናወርሳትን ኢትዮጵያ ዛሬ ለመስራት በወንድማማችነት /በእህትማማችነት ፅንተን እነዚህንና ሌሎችንም ሰው ተኮር ተግባራቶችን በጋራ ትብብር እንድናስቀጥል ጥሪዬን አቀርባለሁ!!!

በዚህ ታሪካዊ ተግባር ፈር ቀሳጅ በመሆን አሻራችሁን ላሳረፋችሁ መሪዎቻችን፣ መጋቢ እናቶች፣ ለድጋ አድራጊዎች እና ይህንን ተግባር በየደረጃው ለምትመሩ እና ለምታስተባብሩ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።



አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ምገባ ኤጀንሲ
Addis Ababa City Administration
Feeding Agency













## ምነወር ኑረዲን አብራር

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ
የግብዓት አቅርቦት ዘርፍ ም/ዋ/ ዳይሬክተር

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ 5 ዓመት በፊት በሀገራችን በተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ እና ህብረ-ብሔራዊ የሆነው የብልጽግና ፓርቲ ምስረታን ተከትሎ በርካታ የለውጥና የሪፎርም ስራዎችን በማካሄድ ቅድሚያ ሰው ተኮር ለሆኑ የልማት ስራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት አብዛኛውን በዝቅተኛ ገቢ ለሚተዳደር የከተማችንን ነዋሪ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስኮች ተጠቃሚ እያደረገ መቆየቱ ይታወቃል።

ከእነዚህ ከተከናወኑ በርካታ ሰው ተኮር ተግባራት መካከል በአብዛኛው ነዋሪ ዘንድ ተቀባይነትና ዕውቅና ያገኘው ተግባር በምገባ ኤጀንሲ አማካኝነት በአዲስ አበባ እና በዙሪያዋ በሚገኙ የመንግስት ት/ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች በቀን 2 ጊዜ ቁርስና ምሳ ዓመቱን ሙሉ የሚሰጠው የምገባ አገልግሎትና የተማሪዎች ደንብ ልብስ፣ የት/ት መርጃ ግብዓት አቅርቦት ስራ በዋናነት የሚጠቀስ ተግባር ነው።

የከተማ አስተዳደሩ በወሰነው ቁርጠኛ የፖለቲካ ውሳኔ መሰረት ወጪው ሙሉ በሙሉ በመንግስት በጀት እየተሸፈነ አገልግሎቱ መሰጠት ከተጀመረበት ከ2013ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ በኤጀንሲው የቀረቡ የተማሪዎች ደንብ ልብስ፣ ደብተር፣ ጫማ፣ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ፣ የመምህራን ጋዋን፣ የመጋቢ እናቶች ማብሰያ ሽርጥ፣ ተጠቃሚዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ሲሆን 452ሺ የነበረው የተማሪዎች ቁጥር ወደ ከ803 ሺበላይ፣ የመምህራን ቁጥር ከ28ሺ ወደ 37 ሺ በላይ፣ እንዲሁም የመጋቢ እናቶች ቁጥር ከ10ሺ ወደ ከ16ሺ በላይ ጨምሮ አገልግሎቱ እየቀረበ ሲሆን አገልግሎቱን ለማቅረብ የወጣው ወጪም በተመሳሳይ ወደ 2 ቢሊዮን ብር ደርሷል።

በመሆኑም የአገልግሎቱ መጀመር በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ የሚስተዋሉ የት/ት ውጤት መቀነስ፣ የተማሪዎች መጠነ ማቋረጥና መድገም እንዲቀንስ ከማድረግ በሻገር በተማሪዎችና በወላጆች ላይ ይደርስ የነበረውን የስነ ልቦና እና ኢኮኖሚያዊ ጫናን በመቀነስ ለነዋሪዎች እፎይታ ከመስጠት አልፎ የነገ ሀገር ተረካቢ ብቁ ትውልድ ግንበታ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል። ይሁን አንጂ ይህ የተማሪዎች ምገባ አገልግሎት በሌላው የዓለም ክፍል የሚሰጥበትን አግባብ ስንመለከት ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገው ወጪ የሚሸፈነው በግለሰቦች፣ በተቋማት፣ መንግስታዊ ባለሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና በዋናነት መጪውን ትውልድ በስነ ምግባርና በዕውቀት የማነጽ የዜግነት ሀላፊነትና ግዴታቸውን በሚገባ በተረዱ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍና ተሳትፎ ሲሆን በከተማችን የሚሰጠው አገልግሎት ከምገባ በተጨማሪ የት/ት መርጃ ግብዓትን ጭምር በማካተት ወጪው ሙሉ በሙሉ በመንግስት እየተሸፈነ የሚቀርብ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የህብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት ማረጋገጥ ይገባል።

በዚሁ መሰረት ይህን የወላጅና ተማሪዎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫና በመቀነስ በትምህርት ዘርፍ ጥራትና በተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ ለውጥ እያስመዘገበ የሚገኝ የተቀደሰ ተግባር በማህበረሰቡ ባለቤትነትና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወጪው እየተሸፈነ አስተማማኝነትና ዘላቂነት ባለው መልኩ በሁሉም አካባቢ ተግባራዊ እንዲሆን የከተማ አስተዳደሩ በቀጣይ በሚዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት እና በሚያደረገው የድጋፍ ጥሪ ላይ በከተማው የሚገኙ የግልና የመንግስት የንግድ ተቋማት ፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የግልና የመንግስት ሰራተኞች፣ እና አጠቃላይ የከተማችን ነዋሪዎች ተሳታፊ በመሆን የሚጠበቅባችሁን የዜግነት ሃላፊነትና ግዴታችሁን እንድትወጡ በከተማ አስተዳደሩ እና በተማሪዎቹ ስም የአደራ ጥሪያችንን እንስተላልፋለን።

“ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ”




## ስንታየሁ ማሞ አለሙ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ም/ዋና ዳይሬክተር ምገባ ዘርፍ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ በአዋጅ 74/2014 ከተሰጡት ተግባራት መካከል የተማሪዎች ምገባ እና የተስፋ ብርሃን ምገባ ማእከላት ማስተዳደር የሚጠቀሱ ሲሆን የከተማ አስተዳደሩ ምገባ ኤጀንሲ እንደ ተቋም እራሱን ችሎ እንዲቋቋም ማድረግ እና ከፍተኛ በጀት በመመደብ ለዜጎች መሰረታዊ ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ ከፍተኛ የአመራር ቁርጠኝነት የታየበት ውሳኔ ነው።

የተማሪዎች ምገባ ፋይዳ በተመለከተ የተማሪዎችን ተሳትፎን እና የመማር ብቃት ከማሻሻል እንዲሁም ለወላጆች እፎይታን ከመስጠት ባሻገር የተማሪዎች አዕምራዊ እድገት /cognitive development/ በማጎልበት ፍተሀዊ የሀብት ክፍፍል ፣ እኩልነትን ፣በተማሪዎች መካከል የተሻለ ማህበራዊ መስተጋብር በማረጋገጥ የነገ ትውልድ አዕምራዊ እድገት የሚፈጥን እና የሚፈጥር እንዲሆን በማድረግ ረገድ ሚናው ከፍተኛ ነው።

በዚህ የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም እስካሁን ከቅድመ መደበኛ እስከ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባ ዙሪያ ሸገር ከተማ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ 701 ሺህ ተማሪዎች ተደራሽ የተደረገ ለ16000 ሺህ በላይ መጋቢ እናቶች የሰራ እድል ፈጥሯል። በቀጣይ የምገባ ስርአቱን ጥራት በማስጠበቅ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል።

ከተስፋ ብርሃን የምገባ ማእከል አንጻር በከተማችን በቀን አንድ ግዜ መመገብ የማይችሉ ዜጎች እንዲመገቡ ለማድረግ በክብርት ከንቲባ አዳነች አበቤ ሀሳብ አመንጪነት ወደ የተጀመረ ሲሆን የከተማውን ማህበረሰብ በማስተባበር ድጋፍ አድራጊዎችን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በአሁኑ ጊዜ በ17 የምገባ ማእከላት 35000 በላይ በእየለቱ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በዚህም የኢትዮጲያዊ እሴት የሆነውን አብሮ የማደግ፣ የመደጋገፍ እሴት የጎለበተበት ተግባር ሲሆን ተመጋቢዎች በየእለቱ ከመመገብ ባሻገር የክህሎት ስልጠና በመስጠት እራሳቸውን ወደ የሚችሉበት እና ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ እየተደረገ ይገኛል። በዚህ ስራ ላይ ሃብታቸውን እውቀታቸውን እያፈሰሱ ያሉ ልበ ቀና ግለሰቦች እና ተቋማት በዚህ አጋጣሚ እያማሰገንኩ በርካታ ባለ ሀብቶች እና ተማት እንዲሳተፉ ጥሪ እናስተላልፋለን።

በመጨረሻም የምገባ ዘርፍ ተግባራት ሁሉም ተቋማት ተሳትፎ እና ቅንጅት የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑ ቅንጅታዊ ስራን በማጠናከር ምገባ ስራው በፖለቲካዊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ የሁሉም ርብርብ በማጠናከር የነገውን ትውልድ እንገንባ።

“ፈጣሪ ኢትዮጲያን እና ሕዝቦቿን ይባርክ”

# ማውጫ


9 ምገባ ኤጀንሲ

12 ተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል

16 የተማሪዎች ምገባ

19 የግብዓት አቅርቦት

22 ከተጠቃሚዎች አንደበት

24 እነማን ምን አሉ

30 ግለ ታሪክ

32 ለግንዛቤ ያህል

36 ፎቶ ማኅደር

ምግብ ኤጀንሲ

# የሃገራዊ ለውጥ ትሩፋት ለአዲስ አበባ

አበባው ፍስሃ

ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ አብዝተው የሻቱት ለውጥ በወርሃ መጋቢት 2010 ዓ.ም አዲስ ክስተት አስተናገደ።

በየክፍለ ዘመኑ በለውጥ መሻትና ፍላጎት መነሾ እንደሃገር በከፋ ደም መፍሠስ በግብታዊነት የ‹‹አብዮት›› መልክ ያለው ጅማሮን ማስተናገድ ቢቻልም አፍርሶ መገንባትና ንዶ መካብ ሆኖብን እኛና ኢትዮጵያ ስንዋትት ቆይተናል።

የ2010ሩ የለውጥ ጅማሮ ሪፎርምን ማዕከሉ አድርጎ፣ ከማፍረስና ከዜሮ ከመጀመር ይልቅ ባለው ላይ መጨመር የተዛነፈውን ማቃናትና አዳዲስ ድሎችን የማስመዝገብ ውጥንን አንግቦ አዲስ ምዕራፍ አዲስ የለውጥ ምጥ ታልፎ በመጋቢት አጋማሽ ተወለደ።

በአዲስ ትርክት፣ በእውነተኛና አካታች ዴሞክራሲያዊ ብዝሃነት፣ ለሁላችንም የምትመችና የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የተጀመረው ሃገራዊ ለውጥ ጉዞ ለአዲስ አበባና ለነዋሪዎቿ በርካታ አዎንታዊ ጅምርን አስከተለ።

ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ በተለያየ የገቢና የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ፣ እንደየ አቅማቸው ህይወታቸውን የሚመሩ ነዋሪዎች ይኖሩበታል።

በተለያየ መነሻ ሠበብ የዕለት ጉርሣቸውን ማሟላት ያልቻሉ፣ የራስንና የቤተሠቦቻቸውን ፍላጎት ማሟላት ያቃታቸው ዜጎችም በከተማዋ ይኖራሉ።

‹‹በመደበኛ የትምህርት ሰዓት በምግብ ዕጦት ምክንያት ተማሪዎች ተዝለፍልፈው ወደቁ››

‹‹በቤተሠቦቻቸው የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛነት ምክንያት ባዶ ምሳ ዕቃ ይዘው የሚመጡ፣ ቁርስ ሣይበሉ ወደ ት/ቤት የሚሄዱ ቢመጡም ምሳ የማይደግሙ ተማሪዎች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ... ጥናቶች አመላከቱ›› የሚሉ ዜናዎችን መስማትና ማየት የሠርክ ሁነት የነበረባት ከተማ አዲስ አበባ ...!

ሣይበሉ ውሎ ማደር፣ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ አንጀት መታጠፍ ... ‹‹ረሃብ ስንት ቀን ይፈጃል?›› እንደሚል ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ... የምግብ እጦት ክፋቱ ... በቃላት አይገለፅም።

የሚበሉትን ማጣት በህፃንነት ለያውም የጨቅላነት ዕድሜና በታዳጊነት ወቅት ሲሆን ደግሞ ይበልጡን ይከፋል ...! ሆድ እየጮኸ፣ በመላ የሰውነት አካል ሃይልና አቅም እያጣ ... ፊደል ለመቁጠርና እውቀት ለመገብየት ተማሪ ቤት መገኘትን፣ ... አስቡት!

እንደሃገር ‹‹የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች!›› ስንል የቆየን ህዝቦች ነን፣ ‹‹ሀገር ተረካቢ፣ ትውልድ አስቀጣይ፣ የኢትዮጵያ የነገ መሪዎች›› እና ወዘተ ለእኛ አዲስ አይደለም።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት አባል ሃገራት በጋራ ተስማምተው ያፀደቁትን የህፃናት መብቶች ኮንቬክሽን በቀዳሚነት ከፈርሙትና ከተቀበሉት የዓለም ሃገራት መካከል አንዷ ነች።

ይህ ዓለም አቀፍ ድንጋጌ ደግሞ የህፃናትን መሠረታዊ መብቶች ማክበርና ደህንነታቸውን ጠብቆ፣ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን አሟልቶ ማሣደግ እንደሚገባ በግልፅ አስቀምጧል።

እናም ታዲያ ...! የልጆቻችንን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ማለት የእለት ተዕለት ምግባቸውን / ሊያውም ለአዕምሮና ለሠውነታቸው ዕድገት የሚረዳ የተመጣጠነ /አሟልቶ ማስተማር የሚሣናቸው ቤተሠብና ወላጆች ቁጥር በተበራከተባት ከተማ በመጋቢት አጋማሽ 2010 ዓ.ም የተበሠረው ለውጥ ትሩፋት ይዞ መጣ!

በ2010 ዓ.ም የክረምት ወራት በሃገራዊ የለውጥ ማዕቀፍ መነሻነት አዲስ አበባን የማስተዳደር ኃላፊነት የተረከበው አዲሱ ሃይል ግዜ ሣይሠጥ ፈጥኖ መተግበር ከጀመራቸው ነዋሪ ተኮር ሥራዎች አንዱ የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም ሆነ!



ወቅቱ እንደ ሃገርም ሆነ እንደ ከተማ የለውጥ ምዕራፍ ጅማሬ በመሆኑ ምክንያት በለውጥ ሂደት ላይ ድጋፍና ተቃውሞ እዚህና እዚያ ቆሞ መወራከብ፣ አዎንታዊና አሉታዊ ስሜቶችና ክስተቶች ከጫፍ ጫፍ የሚታይበት በመሆኑ ይህንን የአዲስ ለውጥ ምዕራፍ አዲስ ውጥን በበጎ የተመለከቱት ባይጠፉም በጥርጣሬ ያዩት፣ ‹‹እንዴት ይሆናል? ›› ብለው ምዕራፉን ከባድነት ይበልጡኑ ያከበዱ በርካቶች ነበሩ።

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ መርሃ ግብርን አስመልክቶ የተሠነዘረ አስተያየት አለምክንያት አልተደመጠም።

በህግና በአዋጅ የተሰጠ መንግስታዊ ኃላፊነትና ተግባር በማስተዳደር ላይ ያተኮረ ሆኖ ዘመናትን በዘለቀበት ሀገር በጎ ውጥን ወጥኖ፤ መንግስታዊ መዋቅርና መሪ /የመንግሥት ከፍተኛ አመራር/ ለየዕለቱ የነዋሪዎች አገብጋቢ ችግር መፍትሄ ይዞ በተግባር መግለፅ እንግዳ ነገር ነው።

ግን የለውጥ ሃይሉ የሃገር ብልፅግና ውጥን ከሠው የተነጠለ አልነበረምና ሁለንተናዊ ብልፅግናዋ የተረጋገጠ ሀገርና ህዝብን የማየት የከፍታ ራዕይ በአዲስ አበባ የአስተዳደሩ ቁልፍ ተግባር ሆኖ ተጀመረ።

በድህነት ውስጥ ያለች ሀገርና ከተማን ለሚመራ አስፈጻሚ መንግስታዊ አካል ዓመታዊ በጀት በህግ አውጪው አካል /ፓርላማ/ (ም/ቤት) ተለክቶና ተዘርዝሮ በሚሠጥባት ከተማ፤ አቅም ያላቸውን አስተባብሮ በመምራት የነገ ተስፋዎቻችንን ዛሬ መገቦ ዕውቀት ለማስታጠቅ አልሞ የለውጥ ሃይሉ ጥሪ አቀረበ፤ ተሣካለትም!

በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን በቀን 2 ግዜ በመደበኛነት እየመገቡ ማስተማሩ የተመጋቢ ተማሪዎችን መሠረታዊ የትምህርት ቁሣቁስ በማሟላት ተጠናክሮ ቀጠለ።

የከተማ አስተዳደሩ ከመደበኛ የመንግሥት በጀት ላይ አንዲት ሣንቲም ሣይነካ በነዋሪዎቿና በትርፋማ ድርጅቶች የበጎነት እገዛ የተጀመረው የምገባ ፕሮግራም ትክክለኛነቱ በተጨባጭ ሲረጋገጥ ውሎ አላደረም።

‹‹ምን ቋጥሬ ት/ቤት ልላክ? ምሣ ምን ይሆን የምበላው? ›› የሚል የተማሪና የወላጅ ጭንቅ ጥብብ አከታተመ፣ በምግብ ዕጦት ምክንያት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተዝለፍልፎ መውደቅ ወደ ነባርነት የመቀየር ጉዞውን ጀመረ።

አስተዋይ መሪ፣ ሀገር ወዳድ ዜጋ የአስተዋይነታቸውና የሀገር ወዳድነታቸው መለኪያ ለነገ ዛሬ ላይ አስተማማኝ በሆነ መልኩ መስራት ነው። እናም በአዲስ አበባ ነገን ዛሬ የመስራት ጥረት በተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር ተገለጠ ...!

የተማሪዎች እውቀት ለመሠነቅ ከትምህርት ቤት በምግብ ዕጦት መቅረት አከተመ፣ የተማሪ መጠነ ማቋረጥና መድገም ከመሠረቱ እየተቀየረ፣ ውጤታቸው ተሻሽሎ የላቀ ክህሎት የጨበጡ ልጆቻችን ቁጥር ሽቅብ መጓዙን ተያይዘው።

በዚህ ሂደት በየዕለቱ በከተማዋ በመንግሥት ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎችን በቀን 2 ግዜ /ቁርስና ምሣ/ መመገብ ‹‹ከባድ ነው፤ አይዘልቁበትም፣ ለታይታ ነው የጀመሩት›› በሚል አነስተኛ ግን ደግሞ አሉታዊ በሆኑ ድምፆች ታጅበ በስኬት ዘለቀ።

መርሃ ግብሩን ወደላቀ ሽግግር ለመጎልበት ያመች ዘንድ ከፕሮግራሙ የወራት ትግበራ በተቀሰመ ተጨባጭ ተሞክሮ በተቋም የሚመራ፣ ወጥነት ባለው ስርዓት በአግባቡ የሚሣለጥ እንዲሆን ለማስቻል የአዲስ አበባ ምገባ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 74/2014 አንደ አንድ የከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካል ተደራጀ።

በዚሁ ኤጀንሲ አማካኝነት የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በየዓመቱ የተመጋቢ ተማሪዎች ቁጥር እያደገ፣ ለመጋቢ እናቶች በተፈጠረ የሥራ ዕድል ጠቃሚነቱ እየጎለበተ በመማሪያ ቁሳቁስ አቅርቦት /የደንብ ልብስን ጨምሮ/ ጥራትና ተደራሽነት እየተሻሻለ በመደበኛ ተግባርነት በስኬት ዘልቋል።

### ዛሬ ...!

በከተማዋ በሚገኙ 777 ቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች 701,000 ያህል የሀገር ተስፋ ተማሪዎቻችን በቀን 2 ጊዜ እየተመገቡ ይማራሉ።

በዚሁ ተግባር በመጋቢነት ሥራ ላይ ለተሰማሩሩ ከ16,000 በላይ እናቶች በ667 ያህል የምገባ ኀብረት ሥራ ማህበራቶቻቸው አማካኝነት ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ተጠቃሚ ሆነዋል።

ለሁሉም በምገባ ፕሮግራም 76 ለሚሆኑ ተጠቃሚ እናቶች በልብስ ስፌት /ጋርመንት/ ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች የደንብ ልብስ አዘጋጅቶ በማቅረብ የገበያና የሥራ ዕድልም መፍጠር ተችሏል።

በስነ ምግብ ሥርዓትና ዓለም አቀፍ የጥራት ስታንዳርዱን በጠበቀ ሣይንሣዊ መስፈርት መነሻነትም የየዕለቱ ምግብ በአግባቡ ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች ይቀርባል።

# ነገን ዛሬ የመሥራት ማሣያ

## የአዲስ አበባ ምገባ ኤጀንሲ




# የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላትን ያዉቁ ኖሯል?

ነጋሽ ዘለቀ

የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላትን በበቂ ሁኔታና በጥልቀት ለማስተዋወቅ ይረዳ ዘንድ ተከታዮችን ጥያቄዎች በማንሳት ማብራራት አስፈላጊ ነው። የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት እንዴት ተጀመረ? መቼ ተጀመረ? ምን ምን አገልግሎት ይሰጣል? ምን ያህል ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል?

## የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት እንዴት ተጀመሩ?

አጋጣሚዎች ታሪክ ይሆናሉ። ታሪክ ይሰራባቸዋል። እንዲህ ሆነ። በአንድ ወቅት ክብርት ከንቲባ አዳነች አበቤ ለሥራ ጉዳይ ሲያመሩ ወደ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቆሼ ተብሎ ወደ ሚጠራው አካባቢ የተመለከቱት ጉዳይ ልባቸውን ነካው።

እዚሁ አዲስ አበባ የእለት ጉርስ የሌላቸው ዜጎች አይጠቅምም ቆሻሻነው ተብሎ ከተደፋው ቆሻሻ ላይ ትርፍራፊ ምግብ ሲመገቡ ተመለከቱ። አጋጣሚ ታሪክ ነው አላልንም ነበር። ይህ አጋጣሚም የአሁኑ የበርካቶች መመገቢያ የሆኑትን የምገባ ማዕከላት ለማቋቋም በር ከፈተ።

ተስፋ ሰጪ በሆኑት ማዕከላት በቀን አንድ ጊዜ መመገብ ለማይችሉ ዜጎች የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል።



## ሚያዚያ 24/2013

የመጀመሪያው የተሰፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል በአራዳ ክፍለ ከተማ ልዩ ቦታው ቱሪስት ሆቴል 200 ሜትር ገባ ብሎ በቻይና ፋወንዴሽን አማካይነት ግንባታው ተሰርቶ ሲጠናቀቅ ምግብ የማቅረቡን ሥራ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመውሰድ በክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተመርቆ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት የመስጠት ሥራው በይፋ ጀመረ።



## አገልግሎቶችስ?

በአዲስ አበባ ከተማ ለከፋ ችግር የተጋለጡና የዕለት ጉርስ የሌላቸው ህፃናት፣ አረጋውያን፤ የአዕምሮ ህሙማን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የጎዳና ተዳዳሪ ሴቶች እና ወጣቶችን በመለየትና በተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት እንዲታቀፉ ተደረገ። በዚህም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማሳተፍ በወጥነት እና በፍትሃዊነት የምገባ ፤የምክርና የማማከር እና ስልጠና አገልግሎት በመስጠት የሚታዩ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚዊ እና ስነ-ልቦናዊ ችግሮችን በመፍታት እና የማህበራዊ ተጋላጭነትን በመቀነስ አምራች የሆኑ ዜጎች እንዲፈጠሩ የማስቻል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።




## ያስገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?

የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል በይፋ ተቋቁሞ ሥራ ከጀመረ በኃላ በተጨባጭ የተገኙ ለውጦች ስንመለከት የተደፋ ምግብን ለማንሳት የተዘረጉ እጆችን በመሰብሰብ ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ፤ በጎ ልብ ያላቸው ባለሀብቶች ድጋፍ ለማድረግ የእርስ በእርስ ትብብር መፍጠር መቻሉ፤ በምግብ እና በተመጣጠነ ምግብ እጥረት ሳቢያ የህጻናትን የጤና ችግር መቀነሱ፣ መጋቢ እናቶች ወቅታዊ የጤና ምርመራ የማድረግ እድል መፈጠሩ፤ ከሰው ተኮር ተግባሮች መካከል በጎ ተፅእኖ እንዲፈጠር መደረጉ፤ የእለት ጉርስ የሌላቸው ሰዎች ተስፋ እንዲኖረቸው መደረጉና ተመጋቢዎችን በሙያ ክህሎት የማነቃቃትና ወደ ሥራ ዓለም እንዲቀላቀሉና እራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ሥራ መጀመሩ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

## ምን ያህል ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል?

ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በ16 የምገባ ማዕከላት በኩፖንና ያለኩፖን የሚመገቡ ከ35,000 በላይ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት በቀን አንድ ጊዜ መመገብ የማይችሉ ዜጎችን ከመመገብ ባሻገር እነዚህን ዜጎች የሚመገቡና አገልግሎቱን የሚያስተባብሩ 310 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

አገልግሎቱ ሰው ተኮር እንደ መሆኑ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተደራሽ ለማድረግ ተጨማሪ የምገባ ማዕከላት በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በመገንባት ላይ ናቸው።




TOP



# የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር

ዮሀንስ ገ/ፃዲቅ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ይህንን የህፃናት መብቶች ስምምነትን በሥራ ላይ ለማዋል እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም ተቀብላ በሀገሪቱ ሕጎችና ፖሊሲዎች በማካተት በመተግበር ላይ ትገኛለች። በዚህም መሠረት የህፃናት መብት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 36፣ በወንጀል ሕግ፣ በትምህርት ፖሊሲ፣ በሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ በማህበራዊ ደህንነት ፖሊሲ፣ በምግብና ስርአተ ምግብ ፖሊሲ፣ በጤና ጥበቃ ፖሊሲ እና በሌሎችም ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መብቶች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው፣ ልጆች በትምህርት ቤት ቆይታቸው ለጤንነታቸው ተስማሚ፣ በንጥረ ምግብ ይዘቱ የተሟላና በቂ ምግብ በማግኘት ከረሃብ ነፃ ሆኖ የመማር መብታቸው እንዳላቸው ያመለክታሉ።

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብርን መተግበር ወላጆች በምግብ ዋስትና ችግር፣ በድህነትና ግንዛቤ ማነስ ምክንያት ከትምህርት ገበታ ውጭ ያሉ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ጠንካራ ማበረታቻ ሆኖ በማገልገል ለዚህ ችግር ቁልፍ መፍቻ መንገድ ባሻገር የተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደግ በአእምሮ የበለጸገ ብቁ፣ ተወዳዳሪና ሀገር ወዳድ ትውልድ ማፍራት ዋና ዓላማው ነው።

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ችግር በልጆች ጤና፣ የመማርና የማሰብ ችሎታ ላይ ተጽዕኖው የከፋ እንደሆነ ይታወቃል። በኢትዮጵያ 16% የሚሆነው የተማሪዎች መጠነ መድገም ከተመጣጠነ ምግብ ችግር ጋር የተያያዘ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ (COHA 2009)። እንዲሁም የተመጣጠነ ምግብ

እጥረት ክስተት በተማሪዎች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ይታያል (ትምህርት ሚኒስቴር 2012)። ከተመጣጠነ ምግብ እጥረትና ከአጭር ጊዜ ረሀብ ጋር ተያይዞ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ስለሚያቋርጡ በርካታ የትምህርት ቀናቶች ይባክናሉ። በርካታ ተማሪዎች በተለያዩ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ምክንያቶች እና በወላጆች ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ የተነሳ ወደ ትምህርት ገበታ ያለመምጣት የመጠነ ማቋረጥና መድገም ሁኔታ በስፋት ታይቷል።

በመዲናችን አዲስ አበባ የትምህርት ቤት ምገባ መጀመር ዋንኛ መንስኤዎች በመንግሥት ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የድሃ ድሃ በሚል ቁጥራቸው አነስተኛ ለሚሆን ተማሪዎች በተለያዩ ድጋፍ ሰጪ አካላት፤ በመምህራንና በበጎ አድራጎት ክበባት አማካይነት የምገባ መርሀ ግብር ሲካሄድ ቢቆይም ምገባው ከፍተሃዊነት፣ ከተደራሽነትና ከቀጣይነት አንጻር ከችግር ያልተላቀቀ ነበር።

የትምህርት ቤት መርሃ ግብር ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳለው በመረዳትና የከተማ አስተዳደሩ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በስጠት 2012 ዓ.ም ጀምሮ ይህንን ሰው ተኮር ተግባር በተሻለና ራሱን በቻለ ተቋም እንዲመራ በኤጀንሲ ደረጃ እንዲቋቋምና በራሱ መዋቅር አደረጃጀት ተፈጠሮለት አገልግሎቱን መስጠት እንዲችል ተደርጓል።

ስለሆነም በኤጀንሲው ለአለፉት አራት አመታት ከተከናወኑ ዋና ዋና ቁልፍ ተግባራት መካካል፤

ከትምህርት ዘርፍ አንጻር ብንመለከት በምገባ ፕሮግራሙ የህጻናትን ተጠቃሚነት በየዓመቱ ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በከተማችንና በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ለሚገኙ ለሁሉም የቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች በየዕለቱ በንጥረ ምግብ የበለፀገ ምግብ በማቅረብ የትምህርት ብክነትን በመቀነስ የተማሪዎችን ውጤታማነት ማሻሻል፣ ጤናማና አምራች ዜጎችን ለመፍጠር ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ሲማሩ ከነበሩት 375,093 ወደ 701,000 ለሚሆኑ ህጻናት የቁርስና የምሳ የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማድረግ በመቻሉ የትምህርት ሽፋንና ተሳትፎን እንዲሁም በትምህርት ገበታ ማቆየት (መጠነ መድገምና መጠነ መቋረጥ) እና የትምህርት ጥራት ማሻሻል ላይ ከፍተኛ የሆነ ለኪት ማስመዝገብ መቻሉ። ከጤና ዘርፍ አንጻር ህጻናት የተመጣጠነ ምግብ በማግኘታቸው በእድሜ እድገታቸው መሰረት አካላዊ /physical/፣ አእምሯዊ /cognative/ና ስነልቦናዊ /psychological/ እድገታቸው ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ መታየት መጀመሩ፣ በግል ንጽህናና ጤና አጠባበቅ ስርዓት ላይ በትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ዘንድ ግንዛቤ እየተሻሻለ መምጣቱ።

ከግብርና ዘርፍ አንጻር ከተማ አቀፍ ግብርና ማጠናከር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተተገበረ መሆኑ፤

የትምህርት ቤት ምገባን በአካባቢው ከሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ከህብረት ሥራ ማህበራት እና ከግሉ ሴክተር ጋር በማስተሳሰር ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የአርሶ አደሩን ገቢና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የምገባ መርሃ ግብሩ በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና በማግኘቱ ሌሎች ተሞክሮ መሆን መቻሉ፤

ለተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ለመስጠት ለተደራጁ ከ16 ሺህ በላይ ለሆኑ ምግብ አቅራቢ እናቶች በሥራ እድል ተጠቃሚ መደረጉ።

## በኤጀንሲው በሶስት አመታት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

**ከትምህርት ዘርፍ አንጻር፦** በከተማችን የሚኖሩ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናት ትምህርት የማግኘት ሰብአዊ መብት እንዳላቸው በመረዳት የትምህርት ተሳትፎ ተደራሽነትን በመሻሻል እና የትምህርት ጥራት የማስጠበቅ ሥራው ቀጣይነት ያለው ለማድረግ በከተማው ስር በሚገኙ የመንግሥት የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በኦሮሚያ ልዩ ዞን በፊንፊኔ ዙሪያ ለሚገኙ ተማሪዎች መንግሥት ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ የምገባ መርሃ ግብር በየቀኑ ይካሄዳል።


በመሆኑም በተማሪዎች ላይ የትምህርት ውስጣዊ ብቃት፣ በትምህርት ገበታቸው ላይ መጠነ ማቋረጥንና፣ መጠነ መድገም መቀነስን እንዲሁም የትምህርት ጥራት ማሻሻል ላይ ለውጥ መመዝገብ ተችሏል።

**ከጤናና ከንጽህና አጠባበቅ አንጻር፦** የተመጣጠነ ምግብ አግኝተው ያደጉ ህፃናት ከሌሎች እቻዎቻቸው ጋር ሲወዳደሩ የበለጠ ጤናማ፣ ውጤታማ በተለይም በሂሳብና በሳይንስ ትምህርቶች የላቀ ችሎታ ያላቸው፣ አዳዲስ ሃሳቦችን ማፍለቅ የሚችሉ፣ የፈጠራ ችሎታቸው የጎለበተ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በትምህርት ተቋማት በየእለቱ በትምህርት ሰዓት የሚወድቁና የሚታመሙ ተማሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል።

ሴት ተማሪዎች በንጽህና መጠበቂያ እጥረት ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው የመቅረት የመቋረጥ ችግሮችን ማስወገድ ችሏል።

**ከሥራ እድል ፈጠራ አንጻር፦** የምገባ ፕሮግራሙ በሁሉም የከተማው ነዋሪ ቤት መግባት የቻለና ከ16,000 በላይ ለሚሆኑ እናቶች የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደረገ መርሃ ግብር ነው።

የከተማ ግብርናን ከማሻሻልን አንጻር የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም የከተማ ግብርናን በትንንሽ ቦታዎች የሚመረቱ የግብርና ምርቶች በተለይ የዶሮና የከብት እርባታ፣ የጓሮ አትክልትና መሰል ምርቶችን በቀን ውስጥ ለበርካታ ትምህርት ቤቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ማቅረብ መቻሉ የግብርና ምርታማነቱን በከፍተኛ ደረጃ አሳድጓል። የአምራቾችንም ገቢና የኑሮ ሁኔታን አሻሽሏል። ለመጋቢ እናቶች ለስራቸው አጋዥ የሚሆኑ የምግብ ግብዓቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በቅርብ ማግኘት በመቻላቸው የተማሪዎችን ምግብ የተመጣጠነና በቂ የንጥረ ምግብ ይዘት ያለው እንዲሆን አድርጓል።



# የግብዓት አቅርቦት ዘርፍ

በኃያም ሰ፲

በግብዓት አገልግሎት ዘርፍ ለተማሪዎች፤ መምህራንና መጋቢ እናቶች እንዲቀርቡ በአዋጅ ላይ የተገለጹ የግብዓት ዓይነቶች ሰባት ሲሆኑ የተማሪዎች ደንብ ልብስ፣ የመማሪያ ደብተር፣ ጫማ፣ የሴት ተማሪዎች ንጽህና መጠበቂያ፣ የመምህራን ጋዎንና፤ የመጋቢ እናቶች ሽርጥ፤ ቦርሳ የመሳሰሉት በዋነኛነት የሚቀርቡ የግብዓት ዓይነቶች ናቸው።

## የተግባሩ አጀማመር /እንዴት ተጀመረ?/

ለግብዓት አቅርቦት መጀመር ዋነኛ ምክንያቱ በመንግሥት ት/ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በት/ቤት የተማሪዎች መለያ ደንብ ልብስ ተግባራዊ እንዲደረግ መወሰኑን ተከትሎ አብዛኛው የከተማችን ነዋሪ ወላጅ በአቅም ማነስ ምክንያት የተማሪ ደንብ ልብስ ፤የመማሪያ ደብተር፤ የት/ት መርጃ ቁሳቁስ እና ምግብን ለማቅረብ በመቸገሩና በተለይ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት መከሰት ችግሩን ይበልጥ እንዲባባስ በማድረጉ በመማር ማስተማሩ ሥራ ላይ መስተጓጎል ከመፍጠር ባለፉ ለተማሪዎች ትምህርት ማቋረጥ፤ ክፍል መድገም፣ በማጋጠሙ ችግሩን ለመፍታት በግለሰቦችና ተቋማት የሚደረገው ጥረት ሁሉም ቦታ ተደራሽ መሆን ባለመቻሉ የከተማ አስተዳደሩ ችግሩን ለመፍታት በወሰደው ቁርጠኛ አቋም ኤጀንሲውን በማቋቋም የተማሪዎች ምገባ እና የግብዓት አቅርቦት ሥራን ከ2012 ዓ/ም ጀምሮ በይፋ እንዲጀመር አድርጓል።

## የአቅርቦቱ ወሰንና የበጀት ምንጭ

አገልግሎቱ የሚሰጥበትና ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በዙሪያዋ በሚገኙ ሁሉም የመንግሥት ት/ቤቶች የሚሰጥ ሲሆን አገልግሎቱ በሚጀመርበት ጊዜ በተለያዩ ተቋማት የበጎ አድርጎት ድርጅቶችና ግለሰቦች ድጋፍ በዓይነትና በገንዘብ በማሰባሰብ ቢሆንም የኮቪድ 19 መከሰትን ተከትሎ በኢኮኖሚው ላይ በታየው ጫና ድጋፍ መቀጠል ባለመቻሉ ከ2013 ዓ/ም ጀምሮ ሙሉ ወጪው በከተማ አስተዳደሩ በጀት በመሸፈን አገልግሎቱ እየተከናወነ ይገኛል።

## የግብዓት አቅርቦቱ ሥራ አጀማመር

የተማሪዎች ምገባ ይሁን የግብዓት አቅርቦቱ ሥራ ከዚህ በፊት ያልነበረ አዲስ ተግባር በመሆኑ ለሚቀርቡት ግብዓቶች የፍላጐት መግለጫ ማዘጋጀት የአምራች ልምድና አቅም ዝቅተኛ መሆን የዲዛይንና የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች በማምረት ችግር ያጋጠሙ ቢሆንም ሙያዊ ድጋፍ ከሚያደርጉ የጨርቃ ጨርቅ ኢንስቲትዩት የዲዛይነር፣ የጨርቅ አምራች እና የቆዳ አምራች ማኅበራትና በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችን በማሳተፍ ለማቅረብ የምከረ ሲሆን ከተማሪዎች ምርጫ ከተስማሚነት ጋር የተያያዙ ችግሮች በማጋጠሙ በቀጣዩ ዓመት ዲዛይን በማሻሻል በርከት ያሉ አማራጮች ተዘጋጅተው የሚመለከታቸው ተማሪዎች ወላጅ፤ መምህራንና ባለሙያዎች የተሳተፉበት ፋሽን ሾው እና በአጭር የጽሑፍ ምልክት በሚከናወን ምርጫ በሸራተን አዲስ ሆቴል

በማዘጋጀት በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ምርጫ ተከናውኖ አሁን እየቀረቡ የሚገኙ የደንብ ልብሶችን በቀጣይነት ወደ ማቅረብ ሥራ ተገብቷል።

## የግብዓት አቅርቦቱ በመጀመሩ ያስገኘው ውጤት

የግብዓት አቅርቦቱ እንዲጀመር መነሻ የሆኑ ችግሮችን ከመፍታትና ውጤታማ ለውጥ ከማስገንዘብ እና የግብዓት አቅርቦት ተግባሩን አላማ ከማሳካት አንጻር ከመማር ማስተማር ሥራ ስኬት፤ ማኀበራዊ ችግሮችን ከመቅረፍ፤ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንጻር የተገኙ ውጤቶች ፡-

- የትምህርት ሽፋንና ተሳትፎ መሻሻል፤ መጠነ መድገምና ማቋረጥ መቀነስ፤ የትምህርት ጥራት መሻሻል
- በጨርቃ ጨርቅ፤ በቆዳ ፤በወረቀት፤ እና በልብስ ስፌት ለተሰማሩ በርካታ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች የገበያና የስራ ዕድል መፈጠሩ፤
- የተማሪ ወላጆችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና መቀነስ መቻሉ፤
- የተቋማት ማህበራዊ ሃላፊነትን የመወጣት ፍላጎት መጨመር እና ማህበራዊ ትስስር መጎልበቱ፤
- በቀን አንድ ጊዜ መመገብ ለማይችሉ ዜጎች የህይወት ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙና የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው በማድረግ የነገን ተስፋ እንዲሰንቁ ማድረግ መቻሉ፤

## ያጋጠሙ ችግሮች

ኤጀንሲው የሚሰጠው አገልግሎት በሀገራችንም ሆነ በከተማችን ልምድ የሌለው ከመሆኑ ጋር ተያያዞ ወደ ተግባር ሲገባ በርከታ ችግሮች ያጋጠሙን ሲሆን ዋና ዋናዎቹ፡-

- በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይል፤ የአሰራር ስርዓት አለመኖር፤
- ምርቱን በጥራትና በጊዜ ሰርቶ ማቅረብ የሚችል አቅም ያለው አቅራቢ አለመኖር፤
- የጥራት፤ ወቅታዊነትና ተደራሽነት ችግር ማጋጠሙ፤
- በተግባሩ ዙሪያ የሚሳተፉ በርካታ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፤
- የማህበረሰብ እና የተቋማት ማህበራዊ ሃላፊነትን የመወጣት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፤

## በቀጣይ የሚተገበሩና ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ተግባራት

ኤጀንሲው የሚሰጣቸው አገልግሎቶች መጀመር በከተማው ውስጥ ይታዩ የነበሩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በመቅረፍ ሰው ተኮር ከሆኑ ስራዎች መካከል የሚጠቀስ እንደመሆኑ መጠን ባለፉት የትግበራ ዓመታት የተገኙ ልምዶችን፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በዝርዝር በመለየትና እየተካሄዱ ከሚገኙ ጥናቶችና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች በመውሰድ የተቋሙን አጠቃላይ የአሰራር የአደራጃጀትና የመዋቅር ማስተካከያ በማድረግ በ2025 ዓ.ም ያስቀመጠንውን ራዕይ ለማሳካት በልዩ ትኩረት የምንሰራ ይሆናል።

## የግብዓት አቅርቦት አፈፃፀምና ሥራ ላይ የዋለ በጀት


አቅርቦቱ ከተጀመረበት ከ2012ዓ.ም ጀምሮ ባለፉት 3 ተከታታይ ዓመታት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የተደረጉ የግብዓት ዓይነቶች ዝርዝር እና በየዓመቱ ሥራ ላይ የዋለ በጀት አፈፃፀም፡-

| ተ.ቁ. | የግብዓት ዓይነት | የተጠቃሚዎች ብዛት | | | የተሰራጨ ግብዓት መጠን /ብዛት/ | | | ሥራ ላይ የዋለ በጀት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | 2014 | 2015 | 2013 | 2014 | 2015 | 2013 | 2014 | 2015 |
| ለአዲስ አበባ ከተማ | | | | | | | | | | |
| 1 | የተማሪዎች ዩኒፎርም | 520,147 | 583,964 | 605,446 | 520,147 | 605,446 | 605,446 | 46,553,1565 | 46,9671,567 | 924,041,583.60 |
| 2 | የመማሪያ ደብተር | 520,147 | 583,964 | 605,446 | 4,054,171 | 4,286,986 | 5,105,559 | 64,461,318.9 | 71,351,135.51 | 101,873,703.34 |
| 3 | የመጋቢ እናቶች ሸርጥ | 9,012 | 10,000 | - | 9,012 | 10,000 | - | 6,218,280 | 7,882,600 | - |
| 4 | የመምህራን ጋዋን | 30,810 | 31,429 | 31,890 | 30,810 | 31,429 | 31,890 | 21,258,900 | 22,686,010 | 25,144,704 |
| 5 | የተማሪዎች ጫማ | 385,549 | 452,556 | - | 385,549 | 381,417 | - | 14,187,8176.51 | 17,777,2369 | - |
| ለፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን | | | | | | | | | | |
| 1 | የተማሪዎች ዩኒፎርም | 161,057 | 194,484 | 198,212 | 161,057 | 194,484 | 198,212 | 144,146,015 | 174,063,180 | 294,154,192.8 |
| 2 | የመማሪያ ደብተር | - | 194,484 | 198,212 | - | 1,263,273 | 1,377,001 | - | 6,884,765.31 | 7,504,576.38 |
| 3 | የመምህራን ጋዋን | - | - | 5,150 | - | - | 5,150 | - | - | 4,060,684.40 |

ተስፋ ብርሃን

# ከተጠቃሚዎች አንደበት

**እሱ ባለው ስዩም**



## ከወላጅ አንደበት

ወ/ሮ ትዕግስት ሙዘሚል

“ በአፍሪካ አንድነት ቁ 1 ትምህርት ቤት በምገባ ስርዓት ውስጥ በት/ቤቱ ዕለት በዕለት የተማሪዎችን ምገባ የመከታተል ኃላፊነት ወስጄ እየሰራሁ አገኛለሁ። በየዕለቱ ተማሪዎችን በቁርስና በምሳ ሰዓት እናሠልፋለን ፤ በቅድሚያ በኬጂ ክፍል የሚገኙ ህጻናት ተማሪዎች እንዲመገቡ እናደርጋለን። ከምገባ በፊት ሁሉም ተማሪ በአግባቡ እጁን እንዲታጠብም እናደርጋለን። በየዕለቱ የምግብ አቅርቦቱን በተመለከተ የተመጋቢ ተማሪዎችን አስተያየት እንቀበላለን ይህ የዕለት ስራችን ነው። ለተማሪ ልጆቻችን በትምህርት ቤታቸው ባልተቋረጠ መልኩ ምገባ መጀመሩ ጥቅሙ በጣም ትልቅ ነው። በዋነኝነት እኛ ወላጆችን አሳርፎናል፣ በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለን፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ የምንመራ ወላጆችን ከምን ላብላ “ጭንቀት ገላግሎ እፎይታን ሰጠቶናል”።


በተለይ በዚህ ት/ቤት ችግረኛም ብቻ ሳይሆን በልመና ለሚተዳደሩ፣ ጎዳና ላይ የሚኖሩ ወላጆች ጭምር ልጆቻቸውን ያስተምራሉ፤ቀደም ሲል ምገባ ከመጀመሩ በፊት ያለውን ሁኔታ ብናስታውሰው ... በዛን ወቅትም ወላጅ ተማሪ መምህራን ህብረት አባል ስለነበርኩ --በወቅቱ በርካታ ተማሪዎች የሚመገቡት በማጣት ይወድቁ ነበር። አሁን ግን ምገባው ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ሳይመገቡ መማር ቀርቷል። ነገ ሀገር የሚረከቡ ልጆች በአሁኑ ሰዓት በተሟላ መልኩ የሚማሩ በመሆኑ ውጤታማና ደስተኛም ናቸው። በተለይ ደግሞ በዚህ ትምህርት ቤት ቀደም ብሎ በኬጂ ደረጃ ለሚማሩት ብቻ ነበር የምገባ አገልግሎት የነበረው ... በዚህ ምክንያት በዛ ወቅት ሌሎቹ ተማሪዎች እንደተገለሉ ይቆጥሩት ነበር፤ አልፎ አልፎም ፀብ ይስተዋል ነበር፤ አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ለሁሉም ተማሪዎች ነው ምገባ እየቀረበ ያለው።

እኛ በወላጅ የተመረጥን የወላጅ ተማሪ መምህራን ህብረት(ወተማህ) አባላት በቁጥር 6 ስንሆን ስድስታችንም የኮሚቴው አባላት ተራ አውጥተን በሳምንት አንድ ቀን በት/ቤቱ በመገኘት ከመግቢያ ሰዓት ጀምሮ በር ላይ ከመምህራንና ከጥበቃ ሰራተኞች ጋር በመሆን ተማሪዎችን እናስገባለ፤ንጽህና መጠበቃቸውን እንቆጣጠራለን፤በምገባ ሰዓት ላይም የምግቡን አዘገጃጀትና አቀራረብ ከመጋቢ እናቶች ጋር በመግባባት የየዕለቱን ምግብ እንቀምሳለን፣ የሚስተካከል ነገር ካለ እንዲስተካከል እናደርጋለን።

እንድ አንድ ወላጆች እንድሁም እንድ አንድ የወተመህ አባል ምገባ ብቻ ሳይሆን የትምህርት መሳሪያቸውን፣ የደንብ ልብሳቸውን፣ ጫማቸውንና ቦርሳቸውን ጭምር አሟልቶ መንግሥት በተለየ ሁኔታ ለድሃው የህብረተሰብ ክፍል የደረሰ፣ ተማሪዎችን ከስጋት እኛ ወላጆችም ከሃሳብና ጭንቀት የገላገለን በመሆኑ ትልቅ ምስጋና ለማቅረብ እወዳለሁ።

# ከተጠቃሚዎች አንደበት

**እሱ ባለው ስዩም**



## ከተማሪዎች አንደበት

ተማሪ ይክረም ሙዜ

በአፍሪካ አንድነት ቀ 1 ትምህርት ቤት መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪ የምገባ ትውስታ

**ከምገባ በፊት፤** ከትምህርት ቤታችን አብዛኛው ተማሪ በምግብ እጦትን እጥረት ምክንያት እራሳቸውን በተደጋጋሚ ይስቱ ነበር፣ የየዕለቱንም ትምህርት በአግባቡ መከታተል የማይችሉም ነበሩ። የደንብ ልብስ በማጣት፣ የአንዱን ከአንዱ መለያየት ይስተዋል ስለነበር ... የማፈር፣ የመሳቀቅና ራስን ዝቅ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ ይስተዋል ነበር

አሁን ... የምገባ አገልግሎት ከተጀመረ በኋላ ...

በፊት በምግብ እጦትና እጥረት የተነሳ በትምህርታችን ላይ በአግባቡ አናተኩርም ነበር። አሁን ያለሃሳብ ሳንጨናነቅ ሙሉ ትኩረታችንን በትምህርታችን ላይ አድርገን እንማራለን ቤተሰቦቻችንንም አናስጨንቅም!እኔ በግሌ ባለፈው አመት በመጀመሪያ ሴሚስተር 11ኛ ወጣሁ፤በሁለተኛው ሴሚስተር ደግሞ አሻሽዬ 6ኛ ወጥቼ ነው ወደ 8ኛ ክፍል ያለፍኩት ... እና ላሳየሁት የውጤት መሻሻል የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆኔ፣ ደብተር፣ የደንብ ልብስ ሙሉ በሙሉ የተሟላልኝ መሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጎልኛል።

ወላጆቻችን በፊት እኛን በየዕለቱ ወደት/ቤት አሟልተው ለመላክ ይጨነቁ ነበር ... አሁን ግን ቁርስና ማሳ እዚሁ ተዘጋጅቶ ስለሚቀርብልን ማታ እራት ብቻ አዘጋጅቶ የማቅረብ ሓላፊነት ብቻ ነው ያለባቸው። የየዕለቱ ምገባችን የተሟላና እንዳይሰለቸን እየተለያየ ነው የሚዘጋጅልን ... በተጨማሪም ተማሪዎች ተዘጋጅቶ በሚቀርብልን የምግብ ዓይነት ላይ አስተያየት እንጠየቃለን። በሰጠነው አስተያየት መስረት ማስተካከያ ተደርጎበት ተሻሽሎ ይቀርብልናል። በየዕለቱ ሽሮ፣ ምስር በጎመን፣ ሩዝ፣ ጨጨብሳ፣ አነባብሮ፣ የሀበሻ ዳቦና የመሳሰሉት በአሪፍ ሁኔታ እየተዘጋጀና እየተቀያየረ ይቀርብልናል። እኔና ጓደኞቼ በየዕለቱ በትምህርት ቤታችን በመመገባችን በጣም ተጠቃሚዎች ነን።

**የወደፊት ምኞት፦** እኔ በግሌ ወደፊት በትምህርቴ በርትቼ ሳይካትሪስት ለመሆን ነው የምፈልገው በተለይ በስነ ልቦና ዘርፍ ሀኪም በመሆን በሀገራችን ብቁ ባለሙያ ሁኜ ለመስራት እመኛለሁ

**ምገባ ባይኖር፦** በትምህርት ቤታችን የምገባ አገልግሎት በይጀመርልን ኑሮ ቀደም ሲል የነበረው የተማሪዎች ራስን ስቶ መውደቅና መታመም፣ ዝቅተኛ ውጤት ማምጣት ይኖር ነበር ይህ ደግሞ በጣም እስከፊ ነው።

**ስለ ተማሪዎች ተሳትፎ፦** እኛ ተማሪዎች መምህራን በየተራ በምገባ ክፍል ገብተው ሲያስተናግዱን እኛም ደግሞ ተመርጠንና ተራ አውጥተን በየደረስን ተራ ቀድመን በመመገብ ሌሎች ተማሪዎች እንዲመገቡ እናደርጋለን። ማለትም ተራ እናስጠብቃለን፣ ምግብ እናድላለን፣ ፅዳት እናጸዳለን፣ እቃዎችን እንሰባስባለን በአጠቃላይ እናስተናግዳለን።

እኛ በየዕለቱ ሶስት ተማሪዎች (በምገባ ክፍል ላይ በተለጠፈልን ተራ መሰረት በመጋቢ እናቶችን እናግዛለን፣ ከመምህራንም ጋርም አብረን እናስተባብራለን።

# እነማን ምን አሉ?

**እሱ ባለው ስዩም**

## የድሆች መጠጊያ

ዕለተ ሰኞ ረፋዱ ላይ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወደ ሚገኘዉ አሙ ዲ ቁ.1 የምገባ ማዕከል አመራን ስንደርስ መላው አባላት የዕለቱን ተመጋቢዎች ለማስተናገድ ደፋ ቀና ይሉ ነበር። እንጀራና ወጡን ማሰናዳት መመገቢያ ሳህኖችን፣ ዉሃ መጠጫ ኩባያዎችን በመልክ ደርደር በትጋት የሚከናወኑ የዕለት ተወዳጅ ተግባራቸዉ አንድ አካል ነዉ።

የሚደረገዉ ቅድመ ዝግጅት እንዳበቃ አስተባባሪውን አቶ አሸናፊን ስራዉ እንዴት ነዉ? ስንል ጠየቅነዉ እሱም በፍፁም የእንግዳ ተቀባይነት ትህትና በፈገግታ ምላሽ ሰጠን። ስራዬን በጣም እወደዋለሁ ምንም እንኳን በየዕለቱ በአማካኝ ከ1000-1400 የሚጠጉ ተመጋቢዎችን ማስተናገድ አድካሚ ቢሆንም ስራችንን በፍቅር ስለምንሰራ ቅንጣት ድካምም ሆነ መሰልቸት አይሰማንም በተለያዩ ችግሮች ተጠቂ የሆኑ የዜጎች የሚመገቡበት ተቋም ማስተዳደርን የመሰለ የሚያኮራ ስራ ባለመኖሩ የአስተዳደር ስራዬን እወደዋለሁ። በተለይ በተመጋቢዎች ላይ በየዕለቱ የምመለከተዉ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ እድገትና የጤና መሻሻልን መመልከት በቃላት የማይተመን ደስታን ያጎናጽፈኛል። በእርግጥ እንደ መብራትና ዉሃ መቆራረጥ የመሳሰሉት ተግዳሮቶች ስራችንን በምንፈልገዉ ፍጥነት እንዳናሳካ እንቅፋት ቢሆኑብንም ተቋሙን ያቋቋመዉ መንግሥትም ሆነ ሚድሮክ ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል። አለን።

ተስፋ ብርሃን

በማዕከሉ ከሚገኙ 40 መጋቢ እናቶች መካከል ወ/ሮ ገነት አለሙን አነጋገርናቸው።

የተቋሙ መቋቋም የእሳቸውንና ከስደት ተመላሽ የሆኑ ጓደኞቻቸውን የሥራ አጥነት ችግር በመፍታት እፎይታ ፈጥሮልኛል። ለመንግሥት በተለይም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምስጋናዬን አድርሱልኝ በተቋሙ አገልግሎት በቆየሁበት 1 ዓመት ከ3 ወር ከፍተኛ የህሊና እርካታ አግኝቸበታለሁ ይላሉ። ጧሪ ቀባሪ አልባ እናቶችን፣ አካል ጉዳተኞችና የኑሮ ክብደት የተጫናቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ማገልገል በዋጋና በገንዘብ የማይተመን እርካታ አጎናጽፎኛል። ከሚመገቡ ወገኖች ቁጥር በላይ የምገባ ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል። መንግሥት ይህንን ፈታኝ መርሃ ግብር እንዳይቋረጥ በሚያደርገው ሁለንታዊ ድጋፍና ጠንካራ የዕለት ተዕለት ክትትል ሊመሰገን ይገባል። ተመጋቢዎች በቋሚነት የሚደራጁበትና ከጠባቂነት ወደ ሥራ ፈጣሪነት የሚሸጋገሩበትን አግባብ መፍጠር ላይ ትኩረት አድርጎ ቢሠራ መልካም ነው ብለውናል። (ፎቶግራፍ)





በምገባ አዳራሹ መስተንግዶ እየተደረገላቸው ከሚገኙት ተመጋቢዎች መካከል ወ/ሮ ትዕግስት ፀጋዬን አነጋገረናቸዋል። ተቋሙ ለኔ ገበና ሽፋኜ የትናንት ጓዳዬ ነው የ3 ልጆች እናት ነኝ። የራሴ የምለው ሥራና ገቢ አልነበረኝም። የልጆቼን አባት ያጣሁት ልጆቼ ህጻን እያሉ ነበር። ለልጆቼ የእለት ዳቦና ጉርስ የምሸፍነው። ሴትነቴን ለአደጋ አጋልጨ የወዳደቁ የፕላስቲክ ጠርሙሶችን በመለቃቀምና በኪሎ በመሸጥ ነው። ይህ ማዕከል የኔና ለ3 ልጆቼ በዕለቱ እጁን ዘርግቶ እያጐረሠ ሽክሜን አቅሎልኛል። ፈጣሪ ለአዲስ አበባ አስተዳደርና ለተቋሙ ሠራተኞች ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ብድራቸውን ይክፈላቸው በማለት ዕምባ እየተናነቃቸው ልባዊ ምስጋናቸውን አደረሱ። (ፎቶ ግራፍ)

ሌላኛው የተቋሙ ተመጋቢ የሆኑትን አቶ ተክሌ ጣፋ ናቸው። ለረጅም ጊዜ በሠሩበት የፀጉር አስተካካይነት ሙያ ባጋጠማቸው የጤና እክል ምክንያት መቀጠል ባመቻላቸው የጓደኞቻቸውን የእርጥባን እጅ ለመመልከት ተገደውና ለከፋተኛ ችግር ተጋልጠው መቆየታቸውን ይናገራሉ። ተቋሙ እምባቸውን እንዳበሰላቸውና የሠው ፊት ከማየት እንደታደጋቸው ይገልጻሉ። (ፎቶ ግራፍ) ይህንን የአቶ ተከሌን ሃሣብ ሌለኛው አዛዉንት ተማጋቢ አቶ ጀማል አባዋሪ ያጠናክሩታል። እኔም 4 ሥራ አጥ ልጆቼን ማጉረስ የቻልኩት ከተቋሙ በተዘረጋልኝ የደግነት እጅ ነው የሃሣቡ አመንጪ የሆነውን መንግሥትም ሆነ ሚድሮክ ኢንቨስትመንትን ከልብ አመሰግናለሁ። (ፎቶግራፍ)



እኛም የተመገቡትን ተመግበን ለተደረገልን አቀባበልና መስተንግዶ ከልብ አመስግነን ልደታ ክ/ከተማ ወደ ሚገኘዉ የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል አቀናን።

የተስፋ ብርሃን ደጆች ወለል ብለዉ ተከፍተዉ እንግዶቻቸዉን በመጠባበቅ ላይ ናቸዉ። በልደታ ክ/ከተማ ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት በቋሚነት የሚሰራዉና የምገባ ማዕከሉን በበጎ ፈቃደኝነት የሚያገለግለዉ ልበ ብርሃን ወጣት ስራ አስኪያጅ አቶ ጌትነት ይበልጣልን እበር ላይ አገኘነዉና በፍቅር የተሞላ አቀባበል አደረገልን። ወደ አዳራሹ ዘለቅን አረፍ እንዳልንም ስለተቋሙ አገልግሎት ሁኔታ ገለፃ እንዲያደርግልን ጠየቅነዉ

“ይህንን ተቋም ሳስተዳድር ማንኛዉንም በደግ ተግባር የሚደሰት ኢትዮጵያዊ የሚሰማዉ ስሜት ይሰማኛል። የህብረተሰቡን ማህበራዊ ችግር የተጋራሁ ይመስለኛል።





በየዕለቱ በአማካኝ ከ700 እስከ 1000 የሚጠጋ ቁጥር ያላቸዉ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ዉስጥ የሚኖሩ የአካባቢያችንን ነዋሪዎች በየዕለቱ እንመግባለን ከእነዚህ መካከል ብዙሃኑ ህይወታቸዉን በጎዳና ያደረጉ ወጣቶችና፣ ጎልማሶች፣ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸዉ አዛዉንቶች፣ እንዲሁም እናቶች እና አካል ጉዳተኞች ሰፊዉን ቁጥር ይይዛሉ።

ጌትነት እሱና መላዉ የስራ ባልደረቦች እያንዳንዱ ተመጋቢ ወደ ተቋሙ ሲመጣ የቤተሰብና የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት እንዲመጣ በትኩረት እንደሚሰሩ ነገረን።

እንደ ሃምሳ አለቃ ኃይሌ እና አቶ በቀለ ታሪክ ያሉ የ91 እና የ83 አመት እድሜ ባለፀጋ የሃገር ባለዉለታ አዛዉንቶችን ቢያንስ አንዴ መመገብ መቻል ከበቂ በላይ ባይሆንም ቢያንስ ያለባቸዉን የኑሮ ጫና በተወሰነ መልኩ ሊያቀል እንደሚችል መረዳት እንዳስቻለዉ ገለጸልን። (ፎቶግራፍ) ጌትነት እንደነገረን ተቋሙ የምገባ አገልግሎት ከመስጠትም ባለፈ ተመጋቢዎችን ከጠባቂነት ወደ ስራ ፈጣሪነት ለማሸጋገር ከተግባረ ዕድ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ት/ቤት ጋር በመነጋገር 163 ያህል ወገኖች ተገቢዉን የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ የመመልመልና ሌሎች የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ ገልጾልናል።

ምስጋናዬን አድርሱልኝ አሉን በዚሁ ማዕከል ዉስጥ በመጋቢ እናቶች አስተባባሪነት የሚያገለግሉት ወ/ሮ የትምወርቅ አሠፋ። “ተቋሙ በተለይ በዝቅተኛዉ የህ/ሰብ ክፍል ከፍተኛ ትርጉም ያለዉ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ገልፀዉ ይህንን ሀሳብ ለሰጡና ለማዕከሉ ስኬታማነት ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት ሁሉ ፈጣሪ ብድራቸዉን ይክፈል በማለት ልባዊ ምስጋናቸዉን አቅርበዋል።



እኛም በመጨረሻ በሁለቱም ተቋማት ያየነዉን እጅግ አመርቂ ስራ በተጨባጭ አረጋግጠን ጉብኝታችንን ቋጨን እዉነትም የምገባ ማዕከላት የብዙዎችን ችግርና የኑሮ ጫና ከማቃለል አኳያ ቀላል ግምት የማይሰጠዉ አኩሪ ተግባር እየፈፀሙ መሆኑን ደምድመን አላማቸዉን ይበልጥ እንዲያሳኩ ያሉባቸዉ ችግሮች በሙሉ መቅረፍ የሚቻልበት አግባብ መፍጠር እንዳለበት አበክረን እናምናለን። በመሆኑም የሚመለከታቸዉን የመንግሥት አካላት ተገቢዉን ድጋፍና ክትትል እንዲያደርጉ አደራ እንላለን።

## የነገ ተስፋዎች

አንድ ዕለት ማለዳ ላይ አንጋፋዋ መምህርት የእደሜያቸውን ሲሶ ባሳለፍበት የፍሬ ህይወት ቁ.1 ት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የተለመደ ተግባራቸውን በመከወን ላይ ሳሉ ድንገት አንድ ድርጊት ቀልባቸውን ይስበውና አይናቸውን ጣል ያደርጋሉ። ተማሪዎች ወደ ክፍል ገብተዋል። የዕለቱ የጠዋቱ የትምህርት መርሃ ግብር የመጀመሪያ ክ/ጊዜ ወደ መገባደዱ እየተጠጋ ነበር። በዛ ጭር ባለው ግቢ ውስጥ አንድ ህጻን ከሚማርበት ክፍል ወጥቶ ትምህርት መሳጭ ወደ አልሆነ ሌላ ክፍል ሲገባ ይመለከቱትና ጉዳዩ ግር አሰኝቷቸው በዝግታ ተማሪዉ ወደገባበት ክፍል ያመራሉ። እንደደረሱም በሩን ከፍተው ሲገቡ አይናቸው ማመን እስኪያቅታቸው ድረስ የተመለከቱትን ነገር አስደነገጣቸው ህጻኑ የ1ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በት/ቤቱ ለአፀደ ህጻናት ተማሪዎች ዘወትር ከሚቀርበው የማለዳ ወተት በብርጭቆዎቹ ውስጥ የቀረውን የመጨረሻ ጭላጭ ወደ ጉሮሮው እያንጠፈጠፈ ጥሙን በማስታገስ ላይ ነበር። ይህን ክስተት በዕለቱ የርህሩዋን መምህርት አንጀት ልክ በሌላው ሀዘን ከመናጡም ባለፈ ለተከታታይ ቀናት ድብርትና ጭንቀትን የፈጠረ አጋጣሚ እንደነበር ዛሬም ድረስ አይዘነጉትም።

እኛም ይላሉ መምህርት ወይንሸት ገ/ማሪያም አሳዛኝ ድርጊት አይኖቸን እንድከፍት አረገኝ። እርግጥ የመንግሥት ትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ከመጀመሩ በፊትም ችግር እንዳለ አውቅ ነበር። ባዶ ምሳ ዕቃ እና የሚቋጠርላቸው ተማሪዎች እንዳለ አውቅ ነበር። ለጤናቸው ተስማሚ ያልሆነ ምግብ ይዘው የሚመጡ ህፃናትን እያየሁ ውስጤ በሀዘን ይደማ ነበር። ለዚህም መፍትሄ ለማበጀት ከስራ ጓደኞቼ ጋር በመመካከር ለራሳችን ከምናመጣዉ ምሳ በተጨማሪ አንድ ምሳ ዕቃ እየቋጠርን ከችግረኛ ህፃናት ጋር በመቃመስ ችግሩን ለማቃለል ጥረት እናደርግ ነበር። ወተቱን ሲጠባ ያየሁት ተማሪዬ ጉዳይም እሱ በድፍረት አረገው እንጅ ሌሎችም የዕሱ አይነቶች ለኖሩ እንደሚችሉ እንድገነዘብ ስለረዳኝ ከስራ ባልደረቦቸ ጋር ተመካክሬ በጣም ለተቸገሩ ተጨማሪ ተማሪዎችም ወተትና ዳቦ የጠዋት ቁርስ ሆኖ እንዲቀርብላቸው ማድረግ ቻልኩ በማለት አይረሴ አጋጣሚዉን አጫውተውናል።

መምህርት ወይንሸት አያይዘውም ከቅርብ አመታት በፊት በመንግሥት የተጀመረው ሁሉም ተማሪ ያካተተ ምገባ ከተማሪዎችና ከችግረኛ ወላጆች ባለፈ ለእንደሳቸው ያሉ የመንፈስና የዕውቀት እናት ሩህሩህ መምህራን ከፍተኛ የመንፈስ ዕረፍት የሰጠ አኩሪ ተግባር መሆኑን አረጋግጠውልናል።

ወ/ሪት ሙሉ እመቤት ደረሰ በልደታ ክፍለ ከተማ የሚገኘዉ ፍሬህይወት ቁ.1የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህርት ሲሆኑ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያሳልጥልኝ ወሳኝ አካል የሆነውን የተማሪዎች ምገባ በከፍተኛ ትኩረት እንደሚከታተሉት ይገልፃሉ።

በት/ቤቱ በየዕለቱ 704 የአንደኛ ደረጃ እና 282 የአፀደ ህፃናት 986 ተማሪዎች ቁርስና ምሳ ገበታ እንደሚቀርብላቸው የሚናገሩት ርዕሰ መምህርቷ መርሃ ግብሩ የዕለት ተዕለት ትኩረትና ክትትል የሚሻ እንደመሆኑ መጠን በት/ቤቱ መምህራንና ሁሉም የድጋፍ ሰጭ ሰራተኛ በፕሮግራም በመደልደል በየዕለቱ የሚያስተባብሩበትን ስልት ከመቀየስ አንስቶ የየዕለቱን የምገባ አይነት ጥራት እስከ መቆጣጠር የዘለቀ ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርጉ ይገልፃሉ።

ወ/ሪት ሙሉ እመቤት ከዚህ በላይ የምገባ ስርዓቱ ያስገኘውን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንደሚከተለው ያብራራሉ። ከሁሉ በላይ የሁሉም ተማሪዎች ዩኒፎርም መልበስ በመካከላቸዉ የነበረውን የልብስና የኑሮ ደረጃ ውድድር እንዳስወገደው ሁሉየሁሉም አጸደ ህጻናትና የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በምገባ ውስጥ በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችል አጉል ፍክክርን በማስወገድ አንዳችም የበላይነትም ሆነ የበታችነት ስሜት እንዳይፈጠር ከማድረጉም በላይ ስነልቦና እንዲዳብር ያግዛል ይላሉ። ከዚህ ሌላ በተለይ

የተማሪዎች የዕርስ በርስ ግንኙነትን ከማጎልበት ባለፈ እንደ አንድ ትልቅ ቤተሰብ የሚተያዩበትን አስደሳች ሁኔታ መፍጠሩን ገልጸው በወላጆች በኩልም ትምህርት ቤቱ የወላጆቻቸው ሁለንተናዊ የዕድገትና የህልቀት ማዕከል መሆኑን እንዲያምኑ ያደረገ መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን አፅንኦት ሠጥተው ያናገራሉ። በመጨረሻም መርሃ ግብሩን ውጤታማ ለማድረግ በትኩረት ለሚሰራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ልባዊ ምስጋናቸውን በመግለጽ ከዚህ በላይ ውጤታማ እንዲሆን ከመንግሥትጋር በጋራ መስራት ይገባል በሚለው አስተያየታቸው ገልጸው ንግግራቸውን ደምድመዋል።

በዕለቱ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ህጻናት ልጃቸውን ሲያደርሱ ያገኘናቸው ወ/ሮ ፈደላ ሁዲ በበኩላቸው በሚለፉት ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ የዘወትር ጭንቀታቸው የነበረውን ለልጄ ምን ላጉርስ የሚል ጭንቀት ምገባው እንደገላገላቸው በእውነተኛ አንደበት መስክረዋል። ዘወትር ልጃቸውን በት/ቤቱ ሲያመጡ አስተማማኝ ወደ ሆነ የደግነትና የእንክብካቤ ቦታ እንደሚያመጡ ሙሉበሙሉ እርግጠኛ ስለሚሆኑ እያንዳንዱን ቀን በደስታና በዕፎይታ እንደሚያሳልፉ በሙሉ ልብ አረጋግጠውልን ይህን ላመቻቸው መንግሥት ና የት/ቤቱ አካላት ምስጋናቸውን ገልጸዋል።

ወ/ሮ እታለማው እንድሪስ የት/ቤቱ መጋቢ እናት ሲሆኑ ህጻናቱ የሚያስፈልጋቸው ነገር ተመዋልቶላቸው በደስታ ሲማሩና ሲቦርቁ ከመመልከት ሌላ ምንም የሚያስደስት ነገር የለም በማለት የሚሰማቸውን ስሜት በፈገግታ ይገልጻሉ። አያይዘውም እኔ ምኖረው በዚሁ አካባቢ እነደመሆኑ የብዙሃኑን ተማሪና ወላጅ የኑሮ ሁኔታ የማወቅ እድሉ አለኝ ስለሆነም በዚህ በት/ቤት በየእለቱ የሚደረገው ምገባ ስንቱን ወላጅ ከጭንቀት እንደታደገና እፎይ እንዳስባለ በቂ ምስክር መሆን እችላለሁ። በዚህም ምክንያት በሚከፈለኝ አነስተኛ ደመወዝ ቅር ሳይለኝ ይልቁንም የህብረተሰቡ ችግር የመፍትሄ አካል እንደሆንኩ በሚሰማኝ መልካም ስሜት እየተጽናናሁ ስራዬን በደስታ እሰራለሁ በማለት አጫውተውናል።

በመጨረሻም በአካባቢያችን ያገኘናቸውን ሁለት ህጻናት ጠርተን ትምህርት እንዴት ነው?ስንል ጠየቅናቸው ህፃን ሐዊ አያና እና አማኑኤል አለምሰገድ ሁለቱም የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ሲያድጉም እሷ ጋዜጠኛ እሱ ደግሞ ዶክተር የመሆን ህልም እንዳላቸው ነግረውናል። ለትምህርትቤታቸው፣ ለመምህራን እና ለጓደኞቻቸው ያላቸው ፍቅር ንፁህ በረዳ ነው ፊታቸው ላይ ይነበባል። እኛ ቅር የሚለን ትምህርት በማይኖርባቸው የቅዳሜና እሁድ ቀናት ቤት ስንውልነው እዚሁ ከጓደኞቻችን የዕውቀትና የገበታ ማዕድ በጋራ እየተቋደስን የምናሳልፋቸው ቀናት ወደር የሌለው ደስታ የምናገኝበት ስለሆነ በት/ቤታችን ደስተኛ ነን በማለት የሚሰማቸውን ስሜት ይገልጻሉ። ከዚህም በተጨማሪ በተለይ የምገባ ስርዓቱ እናቶቻቸው ላይ የስራና የኑሮ ጫና እንዳቃለለ ሁሌም ጠዋት ለእነሱ ቁርስና ምሳ በማዘጋጀት በሚያቃጥሉት ሰዓት ከስራ በማርፈድ የሚፈጠርባቸውን ጭንቀትና ስጋት በማስወገድ እፎይታን እንደፈጠረላቸው በጣፋጭ አንደበት ገለጹልን በአስተዋይነታቸውም አስደመሙን። በመጨረሻም እንዲህ አይነት ምቹ የትምህርት ከባቢና የምገባ ስርዓት ያመቻቹ አካላትንና መምህራንን እናመሰግናለን ሲሉ በንጹህ ልብ የተሰማቸውን ስሜት ገልጸውልን ወደ ክፍላቸው አመሩ። እኛም መልካም ቀንና መልካም የትምህርት ጊዜ ተመኝተን በፍቅር ሸኘናቸው።

ከረፋዱ 4፡30 ሲሆን ተማሪዎችን የእረፍት ስዓት የሚያበስረውን ደወል ሲደወል የጉብኝታችን መጨረሻ ሆነና ሁሉም መምህራን ተሰናብተንና አመስግነን ወደ መውጫው አቀናን በፍሬ ህይወት ቁ.1 ያየነውና የታዘብነው መልካም ተሞክሮ ለሁሉም የሀገራችን ትምህርትቤቶች ቢተገበር ስንል ከልብ የመነጨ የአድናቆት ሃሳብና ምኞታችንን እየተለዋወጥን በተማሪዎች ሳቅና ቡርቃ የደመቀውን ምድር ጊቢ ለቀን ወጣን።

ተስፋ ብርሃን

# ግለ ታሪክ

ጽዮን ገብረማርያም

### የጎዳናዋ ጀግና...

አዲስ አበባ ፒያሳ አወልያ ትምህረት ቤት አጥር ስር አንዲት በሀረግ የተከበበች ትንሽዬ የማዳበሪያ ዛኒጋባ ትገኛለች። ይህቺን ጎጆ ቀልሶ ለመኖር ብዙ መከራን ያሳለፈ ቤተሰብ አሁንም እዚሁ ዛኒጋባ ውስጥ ነው። አንድ ምስኪን እናት ከሶስት ልጆቿ ጋር። በዚህ ጎጆ ለ12 ዓመታት ከደፋሪ ከዝናብና ከብርድ ጋር እየታገለች ልጆቿን ለማሳደግ ዋጋ ከፍላለች። አሁንም የጎዳናን ህይወት ተላምዳ ልጆቿን ለቁም ነገር ለማብቃት ትታትራለች። መቅደስ ትባላለች። ጎጆዋን የጎበኘኋት እንደ ቀልድ በመንገድ ሳልፍ ቢሆንም ሁል ጊዜ በአእምሮዬ የሚመላለስ ጥያቄ ነበረኝ። ይሄን የምላችሁ ከዛሬ 5 ዓመት በፊት ላይ ሆኜ ያየሁትንና ያሰብኩትን ነው። እንደ ቀልድ ከዛኒጋባዋ ደጅ ላይ ዩኒፎርም ለብሰው የሚጫወቱ ሁለት ህጻናትን ነበር ያስተዋልኩት። በአካባቢው ለተቀመጡ ሰዎች ጥያቄ አቀረብኩ *እነዚህ ልጆች የማንናቸው?›› ነገሩኝ። *አሁን እናታቸው የቀን ስራ ጀብሎ ልትሰራ ሄዳለች። የሚኖሩት እዚህ ጎጆ ውስጥ ነው።›› አሉኝ። ጠየኩኝ ተገርሜ እዚህ የማዳበሪያ ጎጆ ውስጥ? *አዎን›› አሉኝ። ከዚያ በኋላ ግን ለአምስት ዓመታት የነዚህ ቤተሰቦች እጣ ፋንታ ምን ይሆን እያልኩ ከማሰብ ውጪ አግኝቻቸውም ሆነ አናግሬያቸው አላውቅም ነበር።

ቤተሰቡን የማግኘት አጋጣሚ የተፈጠረልኝ በ2015 አዲስ አመት ዋዜማ ነበር። የአዲስ አበባ ምገባ ኤጀንሲ ለችግረኛ ቤተሰቦች የትምህርት ቤት ቦርሳ ስጦታ እየሰጠ ነው የሚለውን ዜና ሰምቼ ከዚህ ቤተሰብ ጋር መገናኘትና ስለ ቤተሰቡ ማወቅ ፈለግኩኝ። ያመራሁት ወደ ዛኒጋባዋ ነበር። መቅደስን አገኘኋት የልጆቹን እናት። እነዛ ትንንሽ ልጆች አድገው አገኘኋቸው። መቅደስ ሰው ለማናገር የምትከብድ አይነት ሴት አይደለችም። ወጣትነቷን ሙሉ ጎዳና ላይ ብዙ መከራን እንደተቀበለች ከፊቷ እና ከአይኗ ላይ አይቶ ለመረዳት አያዳግትም።

ታሪክሽን አጫውቺኝ። አልኳት። “ያደኩት በእንጀራ እናት ነበር። እናቴ በህጻንነቴ መሞቷን የሰፈር ሰው ነግሮኝ አባቴን ጠየቅኩት። አዎን ግን ምን ቸገረሽ አርፈሽ ኑሪ አለኝ። እኔ ግን ከልጅነቴ ጀምሮ ይደርስብኝ የነበረው በደል እናትነቷን አምኖ ለመቀበል አላስቻለኝም። እያደግኩኝ ስመጣ ከእንጀራ እናቴ ጋር መስማማት አልቻልንም። በደል መብዛቱ ሳያንስ ጎዳና ላይ ወጣሁ። በተለይ አባቴ ያለርህራሄ አባረረኝ። ጎዳና ላይ እንደወጣሁ ባልና ሚስቶች አግኝተውኝ ወስደውኝ ነበር። ለካስ ለምኜ እንዳመጣላቸው ፈልገው ነበር። ጠዋት ቁራሽ ዳቦ ይሰጡኝና ስለምን ውዬ ማታ ላይ ገንዘቡን እየተቀበሉ ራት እንኳን አያበሉኝም።

ይሄ ኑሮ ሲሰለቸኝ አንዲት ጎዳና ላይ የተዋወኳትን ልጅ አማከርኳት። አዳማ የሚሰራ ስራ አለ ብላ ወሰደችኝ። ስራ አለ ብላ ልታስጀምረኝ ብትወተውተኝም ደፍሬ መስራት ግን አልቻልኩም። መንገድ ዳር ቆሜ ገላዬን ሸጬ ገንዘብ እንድሰጣት ነበር ማድረግ የፈለገችው። አልስማማም በማለቴ ተጣልታኝ አባረረችኝ። ጎዳና ላይ ሳለቅስ ያገኘኝ አንድ የታክሲ ረዳት ግን አዝኖልኝ ገንዘብ እየከፈለ የማዳበሪያ ፍራሽ የሚከራይበት ቤት ያሳድረኝና አይዞሽ ይለኝ ነበር። የልጁ ለኔ ማዘን ከአደጋ እንድጠበቅ ማድረጉ እንድቀርበውና የልብ ጓደኛዬ እንዳደርገው አስገደደኝ። በመጨረሻም ገና በ15 ዓመቴ ከዚህ ልጅ ጋር ተጋብተን አዲስ አበባ መጣን። አጥር ስር በቀየስናት ትንሽዬ የማዳበሪያ ጎጆ ውስጥ ኑሮ ተጀመረ። እኔ መንገድ ላይ ሻይ ቡና እየሸጥኩ እሱ ደግሞ ረዳትነት እየሰራ ህይወት ቀጠለ። በመሀከል አረገዝኩኝ። የመጀመሪያ ልጄን የወለድኩት እዚህ ጎዳና ነበር። ሁለተኛ ልጄን

እንዳረገዝኩ ድንገት ማታ ዝናብ ዘንቦ የተጠጋንበት የግንብ አጥር በመደርመሱ ባለቤቴ ህይወቱ አለፈ። እኔም ድጋሜ ለሌላ ስቃይ ተዳረኩኝ። ሁለተኛ ልጄን ወልጄ አንድ አመት እንደቆየሁ በብርድና ዝናብ ምክንያት ልጄ ታሞ ሞተብኝ። ህይወት ለኔ ከባድ ነበር። ሳግ አቋረጣት። “እኔንና ሴት ልጄን የመንገድ ላይ ሰካራምና ጥጋበኛ ወንዶች ለመድፈር በተደጋጋሚ ሞክረዋል። እንቅልፍ አላውቅም ነበር። ምክንያቱም እኔና ሴት ልጄ እንዳንደፈር።” ብላ እንባዋን አፈሰሰች። የመቅደስ ሳግ የተሞላበት ንግግር ያማል። አረጋጋኋት ጨዋታዋን ቀጠለች። “ይሄንን ችግር ፍራቻ አገባሁ። ሁለት ልጆችን ወለድኩ ሆኖም ትዳሩ የተሳካ አይደለም። ምንታደርጊወለሽ ጎሽ ለልጆቿ ስትል ተበላች።” አለችኝ።

አሁን ምን ላይ ነሽ? “አሁንማ ከበፊቱ በተሻለ ለልጆቼ ትምህርት ቤት የሚሆን እድል አለ። ምን መሰለሽ ድሮኮ ልጆቼ ምግብ ሳይበሉ ይማሩ ነበር። ካገኘን በልተን ካጣንም ተርበን ነበር። አሁንማ ያ ቀረ። ልጆቼ ማግብ የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ ቦርሳና የመማሪያ ቁሳቁስ ያገኛሉ። እሱ ለኔ በጣም ረድቶኛል። እስከመጨረሻው ተስፋ ጥያለሁ። ልጆቼ ተምረው ለቁም ነገር ይበቁልኛል አምናለሁ። አንድ ቀን እኔም እንደ ሰው ሙሉ ሆኜ እቆማለሁ ተስፋ አለኝ።” አለችኝ። እኔም ስለመቅደስ ለምገባ ኤጀንሲ ሃላፊዎች ነግሬያቸው ነበር። በወቅቱ ለሶስቱም ልጆቿ የደብተር መያዣ ቦርሳዎችና የመማሪያ ቁሳቁሶች ሰጥተዋታል።

አንባቢዎቼ ሰፊዋ አዲስ አበባ ላይ እንደ መቅደስ አይነት በርካታ እናቶች አሉ። እንባቸው በምገባ የታበሰላቸው። መቅደስ ወደ ፊት ህልሟ ተሳክቶላት የልጆቿን ክብር ለማየት እንድትበቃ ተመኝቼ ስሟን የጎዳናዋ ጀግና ብዬ ሰይሜላት የምገባ ኤጀንሲውንና የከተማ አስተዳደሩን አመስግኜ ልሰናበት።





# ለግንዛቤ ያህል

ጽዮን ገብረማርያም

## 1. ልዩ ልዩ ጠቃሚ መረጃዎች

### የምግብ እጥረት በሽታ በምን ይከሰታል?

ተመጣጠነ የምግብ እጥረት የሚመጣ የህፃናት በሽታ ኳሾኦርኮር የሚል ሳይንሳዊ ስያሜ አለው።ሰውነታችን ስራ ለመስራት እንዲሁም የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ከምግብ የሚገኝ የሰውነት ጉልበት (calories)፣ ገንቢ ምግብ (protein) አጠቃላይ ምግብ ያስፈልገዋል። በተለይም በህፃናት ላይ ችግሩ በጣም ከባድ ስለሆነ በችግሩ ግንባር ቀደም ተጠቂዎች ናቸው።

ነገር ግን ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ ካላገኙ ጡንቻቸው እና አጥንታቸው ይሳሳል። በዚህም ምክንያት በቀላሉ ሊሰበር ይችላል።

አስተሳሰባቸው ይደበዝዛል የማሰብ ክህሎታቸው ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጠራል።

### ምን መደረግ አለበት?

በሽታው ሳይከሰት በፊት ለልጆቻችን የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ታላቅ መፍሄ ይሆናል። በተለይም እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት እንደ አሳ ባቄላ አተር ስጋ እንቁላል ወተት ጥራጥሬዎችን እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ የመሳሰሉ ምግቦችን መመገብ አስፈላጊ ነው።

በተለይም የህፃናት ሰውነት ገንቢ ምግብ (protein) በከፍተኛ መጠን ይፈልጋል። በቂ የሆነ ገንቢ ምግብ ያላገኘ ሰውነት በቀላሉ በበሽታ ይጠቃል። ስለዚህም ህፃናት በቂ የሆነ የተመጣጠነ ምግብ ካላገኙ ሰውነታቸው በምግብ እጥረት ህመም ይጠቃል። ይህም በቀላሉ እስከ ሞት ሊያደርሳቸው ይችላል።

አንዱ የምግብ እጥረት ህመም የሚከሰተው ከገንቢ ምግብ እጥረት ነው። ይህም የገንቢ ምግብ ሃይል እጥረት ህመም (protein energy malnutrition) በመባል ይታወቃል።

ችግሩን በቀላሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመቅረፍ አስቸጋሪ ስለሆነ ህፃናት ገንቢ ምግብ ሰውነታቸው በሚያስፈልገው መጠን መመገብ ያስፈልጋል። አንዴ በሽታው ከተከሰተ ህፃናቱ ከህመሙ ለማገገም ረጅም ጊዜ ይወስድባቸዋል።

**ምልክቶቹም፦** የሰውነትና የሆድ ማበጥ፣ የህፃናት እድገት መቆም ወይም ክብደት አለመጨመር፣ ሰውነት መቁሰል እና የሰውነት ሽፍታ፣ ፀጉር መነቃቀል እና ሌሎችም

ምንጭ፦ ከተለያዩ የህክምና መጽሀፍት የተገኘ

## 2. የሳይኮሎጂ እውነታዎች

አስገራሚ የሆኑ የሳይኮሎጂ (Psychology) ግኝቶችና እና እውነታዎች

1) እቅድዎትንና አላማዎትን ለሌሎች ከነገሩ ያንን እቅድ የማሳካት እድልዎ ይቀንሳል:-

በፈረንጆች አቆጣጠር ከ1933 ዓ/ም ጀምሮ በተደረገው ጥናት መሰረት አንድ ሰው እቅዱን ለሌላ ሰው ከነገረ እቅዱን ስለነገረ የሚሰማው እርካታ ባይነግር ኖሮ የሚኖረውን ግፊት እና እልህ ይቀንስበታል ብሎ ጥናቱ ያሳያል።

2) ብዙ ሰዎች አንድን ሙዚቃ በጣም የሚወዱት ያሳለፉትን ስሜታዊ ጊዜ ስለሚያስታውሳቸው ነው:-

ሙዚቃ ስሜት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ ተቃራኒውም እውነት ነው። ያማለት ስሜት ዘፈንን እንድንወደው ወይም እንዳንወደው ተጽእኖ ያደርጋል።

3) ሙዚቃ ስለ ማንኛውም ነገር ያለን አመለካከታችን ላይተጽእኖ ያደርጋል በ Groningen University በተካሄደው ጥናት መሰረት ሙዚቃ አመለካከታችን ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

4) ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ገንዘብን ለሌሎች ሰዎች ጥቅም ላይ ማዋል ለራስ ከማዋል የበለጠ ደስታን ይሰጣል:- በ Harvard Buisness School በተደረገው ጥናት ገንዘብ የሚሰጡ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ገንዘብ ከማይሰጡ ይልቅ የበለጠ የሚሰጡ ደስተኞች ናቸው።

5) በጥናቶች መሰረት ገንዘብን ንብረት ማካበት ላይ ከማዋል ይልቅ በተግባራዊ ነገሮች ላይ ማየት የበለጠ ደስተኛ ያደርጋል

6) አሁን ባለንበት ዘመን የሚኖሩ በርካታ ልጆች በተለይ ምዕራባዊያን እንደ ኤውሮፓውያን አቆጣጠር በ1950 ዎቹ ከነበሩት የአእምሮ ህመምተኞች ተመሳሳይ መጠን ያለው ጭንቀት አለባቸው

ለዚህ ምክንያት ከሆኑት አንዳንዶቹ ሱሰኛ መሆን፣ ከህብረተሰቡ ጋር ብዙ ተቀራራቢነት አለመኖር፣ ስራ መቀያየር፣ የኑሮ ቦታ መቀያየር ይጠቀሳሉ። አንዳንድ እንደ ፀሎት እና ቤተ ሀይማኖታዊ ስርዓት መከታተል የአእምሮን ጭንቀት ይቀንሳሉ

8) ገንዘብ ደስታን ሊገዛ ቢችልም ከተወሰነ የገንዘብ መጠን ካለን በኋላ ግን መጨመሩ ደስታችን ላይ ብዙም ለውጥ አያመጣም

9) በደስተኞች ሰዎች እራሳችንን መክበብ ወይም ከደስተኞች ጋር ብዙ ጊዜ አብሮ መሆን ደስተኛ እንድንሆን ያደርገናል

10) ከ 18 እስከ 33 አመት ዕድሜ ያላቸው ሰዎች ከየትኛውም ዕድሜ ክልል ካሉ ሰዎች የበለጠ ጭንቀት አለባቸው። ከ33 አመት በኋላ የጭንቀት መጠን እየቀነሰ ይሄዳል።

ምንጭ፦ ከልዩ ልዩ መጽሀፍቶች የተወሰደ



## 3. ድብርት

ልክ እንደ ማንኛውም አካላዊ ሕመም ስኳር፣ የኩላሊት ህመም አልያም ወባ አይነት የአዕምሮ በሽታ ሲሆን፤ በማንኛውም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችልና ተገቢው ህክምና ከተደረገለት መዳን የሚችል በሽታ ነው።

ይህ ሕመም ከሰዎች ጋር አብሮ ለረዥም ጊዜ የሚኖርና ከባድ የሆነ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የአዕምሮ በሽታ ነው።

የዓለም ጤና ድርጅት በአገርም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ለረዥም ጊዜ በመቆየት ጉዳት ከሚያደርሱ እንደ ስኳር ካሉ በሽታዎች መካከልም አስቀምጦታል።

የድብርት መንስኤዎች

ለበሽታው መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

‘’የሚወዱትን ሰው በሞት ከማጣት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ከባድ ሀዘን፣ የሰውነታችንን ተፈጥሮአዊ አሰራር የሚረብሹ ሕመሞች፣ የአእምሮ ሰላምን የሚነሱ እንደ አካላዊ እና ጾታዊ ጥቃቶችን የመሳሰሉ ጉዳቶች፣ የገንዘብ እጥረትን የመሳሰሉና ሌሎች ማህበረሰባዊ ጫናዎችም እንዲሁም በአንድም ሆነ በሌለ መንገድ ራስን ከማህበረሰቡ ማግለል ለከፍተኛ የድብርት ሕመም ሊያጋልጠን ይችላል።

በሌላ በኩል ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ሴቶች ላይ ተለይቶ ከልጅ መውለድ ጋር ተያይዞ በእርግዝና ወቅት አልያም ከወሊድ በኋላ ድብርት ሊያጋጥም ይችላል።

የአካል ጉዳተኞች እና ቤተሰቦቻቸውም ቢሆኑ ለድብርት የመጋለጥ እድላቸው ከፍ ያለ ነው።

የድብርት ምልክቶች


ለተከታታይ ረጅም ጊዜ የሚቆይ የድብርት ስሜት፣ መሪር የሆነ ሀዘንና ለሁሉም ነገር ፍላጎት ማጣት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከእነዚህ ምልክቶች በተጨማሪ ከዚህ በፊት ከእንቅልፋችን ተነስተን ስናደርጋቸው ጥሩ ስሜት ይፈጥሩልን የነበሩ ነገሮች ደስታን መስጠት ማቆም ብቻ ሳይሆን ከነጭራሹ ሊያስጠሉን እንደሚችሉ ሀኪሞች ይናገራሉ።

ማንኛውም ሰው የአእምሮ ጤና መታወክ ሊገጥመው ይችላል ምክንያት የሌለው ጭንቀት፣ የባዶነት ስሜት፣ ደጋግሞ ራስን መውቀስ፣ ምንም የማልጠቅም ሰው ነኝ እያሉ ማሰብ፣ ተስፋ መቁረጥ፣ የሚረዳኝ ሰው የለም ብሎ ማሰብ፣ ከባድ ድካምና አቅም ማጣት፣ የእንቅልፍ መዛባት ወይም በጣም መተኛት አልያም እንቅልፍ ማጣት፣ ስራና የግል ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማጣት እንዲሁም የምግብ ፍላጎት መቀነስ ዋነኛ ምልክቶቹ ናቸው።በዚህ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ከሌላ ጊዜው በተለየ መልኩ ደብሯቸው ስንመለከት ወይንም ራሳቸው ደብሮኛል ብለው ሲናገሩ በቀላሉ አይተን ማለፍ የለብንም።

ተገቢውን ድጋፍና ሕክምና እንዲያገኙ ማበረታታት አለብን። አለበለዚያ እነዚህ ሰዎች በጊዜ ብዛት እራሳቸውን ወደ መጥላትና ራስን እስከ ማጥፋት ሊደርሱ ይችላ

ምንጭ፦ የአማኑኤል ሆስፒታል ድረ-ገጽ





# አዲስ አበባ በዓለም አደባባይ ደምቃ እንድትታይ ስላደረጋችሁ እናመሰግናለን!!

“የተሰጠን እውቅና ለላቀ ስራና ለበለጠ ውጤት በአብሮነት እንድንነሳ ያተጋናል!!” በሚል መሪ ቃል አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም (Milan Urban Food Policy Pact) እና C40 የከተሞች የአየር ንብረት ጉባኤ የበካይ ጋዝ ያስቀረ ተዘዋዋሪ ኢኮኖሚና የቆሻሻ አጠቃቀም ስርዓትን በመዘርጋት ላገኘችው እውቅና በዛሬው እለት በሚሊኒየም አዳራሽ በተዘጋጀው የእውቅናና ማበረታቻ ስነስርዓት በድምቀት ተጀምሯል።

የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራማችን ከዚህ ቀደም ተማሪዎች በርሃብ ይወድቁ ከነበረበት ሁኔታ ወጥተው በርካታ ተማሪዎች በተረጋጋ ሁኔታ የሚማሩበት ፤መጠነ ማቋረጥ የቀነሰበት፤ የውጤት መሻሻል የታየበት፤ ወላጆች ከብዙ ጭንቀት እፎይ ያሉበት ፕሮግራም ነው።


የአዲስ አበባ ከተማ የተሸለመችው በተማሪዎች ምገባ ቢሆንም፤ በቀን አንድ ጊዜ እንኳን ምግብ ለማግኘት የሚቸገሩትን ዜጎች 13 ምገባ ማእከላትን በመገንባት በቀን በአማካኝ 30ሺህ የሚደርሱ ዜጎችን እየመገበች መሆኑ ይታወቃል።





# የሰራተኞች ፎቶ













ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሲመገቡ














# የመጋቢ እናቶች ፎቶ












የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት ተጠቃሚዎች ሲመገቡ







# የተስፋ ብርሃንምገባ ሴት ተጠቃሚዎች በስልጠና ላይ










# የተስፋ ብርሃንምገባ ሴት ተጠቃሚዎች በስልጠና ላይ

### 1ኛ ዙር ምርቃት







# የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት ጉብኝት

ወጣቶችና የሴት ሊግ አመራሮች




የአዲስ አበባ የሃይማኖት አባቶች










የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት ምርቃት

















ADDIS


MAYOR

OFFICE



MAYOR

OFFICE
MAYOR

OFFICE






OFFICE


MAYOR














በኦሮሚያ ክልል የተማሪዎች ምገባ ጉብኝት





# የእውቅናና ሽልማት (8ኛው የአፍሪካ የምገባ ቀን)













# እናመሰግናለን

የወላጆቻችንን ጭንቀት ያቃለለ፣
ከምሳ ዕቃው ሰቀቀን እፎይ ያስባለ።
ምገባ ተጀምሮ በመንግስታችን፣
ትምህርታችን ላይ ብቻ ሆኗል ትኩረታችን።

የወላጆቻችንን ጭንቀት ያቃለለ፣
ከደንቡ ልብሱ ወጪ እፎይ ያስባለ።
ምገባው ሁሉን ነገር አሟልቶልናል፣
እንደ ወላጆቻችን እኛም ደስ ብሎናል።

ሁሉን ስላረገልን ያለ ሀሳብ በትኩረት
ተግተን እንድንማር፣
እናመሰግናለን የት/ ቤቶችን
የምገባ ተግባር።

የወላጆቻችንን ያሳብ ሸክም አቃሎ
ስላስደሰታቸው፣
እናመሰግናለን መንግስትን በእነሱ ስም
እኛም ልጆቻቸው።

እናመሰግናለን አሁንም ደጋግመን -- ደጋግመን፣
እኛ ነን የምናውቀው ምገባው ምን እንደጠቀመን
እኛም ቃል እንገባለን በእውቀት ታንፀን በእውቀት
እንደምናሳያችሁ - በተግባር - የኢትዮጵያን እድገት

ኑሮን ለመቋቋም የቸገረው አቅም፣
የተማሪዎችን የምገባ ጥቅም።
ሰሀን ለመቋጠር አቅም ያጡት እጆች፣
ጭንቀትና ሀሳቡን ያውቁታል ወላጆች።

ሁሌ በየአመቱ ትምህርት ሲከፈት፣
የደብተር የቦርሳው የወጪውን ጭንቀት።
እንዴት እንደነበር ወላጆች ያውቁታል፣
ዛሬ ያ ሁሉ ሀሳብ ሰቀቀኑም ቀርቷል።
እናመሰግናለን ስለመገባችሁን እናመሰግናለን
“ስላለበሳችሁን”
ምገባው እንዲቀጥል አደራ እንላለን።
ሁሌም እንዳይቋረጥ አደራ እንላለን።